# ሙስናን ለመከላከል እርምጃ መውሰድ




## በወጣቶች ለወጣቶች የተዘጋጀ ደረጃ በደረጃ ቱልኪት



United Nations
Office on Drugs and Crime

GRACE

YouthLED



# ሙስናን ለመከላከል እርምጃ መውሰድ

በወጣቶች ለወጣቶች የተዘጋጀ
ደረጃ በደረጃ ቱልኪት

©2024 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል መከላከል ጽህፈት ቤት (ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ)

የሚመከር አጠቃቀስ (ሳይቴሽን)፡ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ 2024. ሙስና ላይ እርምጃ ስለመውሰድ፡በወጣቶች ለወጣቶች የተዘጋጀ ደረጃ በደረጃ መመሪያ

በዚህ ህትመት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ስያሜዎች እና አቀራረብ በዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ በኩል የማንኛውም ሀገር፣ ግዛት፣ ከተማ፣ አካባቢ ወይም የነዚህን ባለሥልጣናት ህጋዊ፣ የልማት ሁኔታ፣ የድንበር ወይም የወሰንን በተመለከተ ምንም አይነት አስተያየት መስጠትን አያመለክትም።

አርታኢ፡ ጀኒ ሞርጋን

ዲዛይን እና ኢሉስትሬሽን፡ ሪዲሂ ቫኪል

በዚህ ህትመት ውስጥ ያለውን ኮንተንት መጠቀም፣ ማባዛት እና ማሰራጨት በዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ የሚደገፍ ነው። በህትመቱ ውስጥ በግልፅ ካልተገለጸ በስተቀር ህትመቱ ለግል ጥናት፣ ለምርምር እና ለማስተማር ዓላማዎች ወይም ለንግድ ላልሆኑ አገልግሎቶች ኮፒ ፣ ዳውንሎድ እና ፕሪንት ሊደረግ እና ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፤ ይህም ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲን እንደ ምንጭ እና የቅጂ መብት ባለቤት ተገቢውን እውቅና ከተሰጠው እና የተጠቃሚዎችን እይታዎች፣ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች በምንም መልኩ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ የማይደገፍ ከሆነ ብቻ ነው።

ማስታወቂያ፡- ይህ ቱልኪት መደበኛ አርትዖት ያልተሰራለት ሲሆን በዚህም ምክንያት ጥቃቅን ስህተቶች ሊገኙበት ይችላል። መመሪያው ወደ ሌሎች የተባበሩት መንግስታት ኦፊሴላዊ ቋንቋዎች እንዲሁም ወደ ፖርቹጊዝ፣ አልባኒያን፣ ሄይቲ ክሪኦል እና ማላጋሲ ተተርጉሟል። ቱልኪቱ የተዘጋጀበት ኦሪጂናል ቋንቋ ኢንጊሊዘኛ ሲሆን ሌሎቹ ቋንቋዎች ለመረጃ እና ለተደራሽነት አገልግሎት ብቻ የቀረቡ ናቸው። ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ ይህንን የቱልኪት እትም ለመተርጎም ላደረገችው ጥረት ለኑኃሚን ጥበቡ በለጠ ምስጋናውን ያቀርባል።

# ምስጋና

ይህ ህትመት የተዘጋጀው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል መከላከል ጽህፈት ቤት (ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ) ነው።

ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ በጥልቅ ምስጋና ለዚህ ሕትመት አዘጋጆች እውቅና ይሰጣል። እንዲሁም ለዚህ ፕሮጄክት ላበረከቱት እውቀት፣ ለሰጡት ጊዜ እና በበጎ ፈቃደኝነት እና በፀረ-ሙስና ተግባር ላሳዩት ቁርጠኝነት ያመሰግናቸዋል። የዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ YouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ (2021-2023) አባላት ማለትም ኡቼኩን አብዱጋንየቭ፣ ኤስማ ጉምብርእድዜ፣ ማክስ አማኑ፣ ዳንያ አሞንዲ ፓሻ፣ ፀንጉንብሌግ ናራንቹሬቭ፣ ኤድዋርዶ አንቶኒዮ ዳ ሲልቫ ፊጌሬዶ፣ ኤሊሳ ኦርላንዶ፣ ሴራና ኢብራሂም፣ ሳላሃልዲን አላዛይዜህ፣ ኢሳያ ቶማስ፣ ታኒያ ቢትሪዝ ቤሎ ሬጋላዶ፣ ሎግማን ኦስማን አህመድ አልሃግ፣ ካሚላ ፍሎሬንሺያ ቶርት፣ ራፋኤል ኦሊቪዬራ ሌይት፣ ፕሪክሽያ ቢማሊ፣ ካንሃይያ ቫርሽኒ፣ ቡዪ ይ ንሂ፣ ዴክስተር አርቪን ኢ ያንግ፣ ስይልቬን ኦቤዲ ካኢንድ፣ ካንሃይያ ቫርሽኒ፣ ካቪሻ ፒላይ፣ አኢሜ ሉዶቪች ፔግድወንዴ ሳዋዶጎ፣ ፓርኔህ ቲ ማሎቤ ምስጋናውን ያቀርባል።

ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ በዚህ መመሪያ ስራ ጊዜያቸውን፣ እውቀታቸውን እና ልምዳቸውን ላበረከቱት ሁሉ ምስጋናውን ያቀርባል።

ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ ለሮቤርታ ፋልቮ፣ ቢያንካ ኮፕ፣ ሊዮናርዶ ፓራዲሶ እና ኤሪክ ኦርቴጋ ሪኮ አጠቃላይ ቅንጅት እና የመመሪያውን ተጨባጭ ግብ በማረጋገጥ፣ የYouth-LED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ አባላትን ስራ በማስተባበር፣ የይዘት ምርምር እና ግምገማ እንዲሁም ይህን ህትመት በጋራ በማዘጋጀታቸውምስጋናውን ያቀርባል።

ይህ ህትመት ከዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ የሙስና እና የኢኮኖሚ ወንጀል ቅርንጫፍ ቡድን የተደረገውን ጠቃሚ አስተዋፅዖ እንዲሁም ይህን ህትመት የገመገሙትን ካሪ አን ሉካስ፣ ኤሚሊያ ሩኢዝ ማርቲኔዝ፣ ሜላኒ ቻበርት፣ ዳኒዬላ ሶታ ቫሊዲቫ፣ ጁሊያ ፒሊግሪም፣ ሳብሪና ዳ'አንድሬአ፣ ጄኒፈር ሳርቫሪ-ብራድፎርድ፣ ዢያኦሆንግ ሊ እና ብሪጊቲ ስትሮብል-ሻው ምስጋናውን ያቀርባል።

ምስሎች: © p. 24: aestheticssofcrisis ; p. 25: Beth/flickr .; p 32: RedEscolas.

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተተው መረጃ ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰበ ሲሆን እነዚህም ከዓለም ዙሪያ ካሉ ወጣቶች ጋር እና በመካከላቸው ከተደረጉ ውይይቶች እንዲሁም በታዋቂ ሚዲያዎች የታተሙ ህትመቶችን ከመገምገም የተገኘ መረጃን ጨምሮ ሲሆን ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተገደበ ነው።



# ይዘቶች


ስለ ቱልኪቱ 2

ቱልኪቱን የጻፈው ማን ነው? 2

ቱልኪቱ ለማን ተፃፈ? 3

የወጣቶች የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭን ለማዳበር 10 እርምጃዎች 4

01: እራሳችሁን አስተምሩ 5

02: ትኩረት የምታረጉበትን ጉዳይ ምረጡ 9

03: አውዳዊ አገባብ አድርጉ 18

04: ንድፍ አውጡ 20

05: የፈጠራ ችሎታችሁን አጠናክሩ 23

06: አጋሮችን አግኙ 27

07: አካታች ሁኑ 29

08፡ ደህንነታችሁ የተጠበቀ ይሁን 31

09: ሌሎችን አስተምሩ 31

10: ይተግብሩ! 32

የመጨረሻ ጠቃሚ ምክር፡ ስራችሁን መገምገምና ያመጣውን ለውጥ ለሌሎች ማሳወቅን አትርሱ 37

ቀጥሎ ምን አለ? 39

# ስለ ቱልኪቱ

ይህን እያነበባችሁ ከሆነ ሙስና በህይወታችሁ፣ በማህበረሰባችሁ ወይም በሀገራችሁ ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ በመሆኑ ትጨነቃላችሁ፤ እናም በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ነገር ማድረግ ትፈልጋላችሁ።

በሙስና ላይ እርምጃ እንዴት እንደሚወስዱ ወደ YouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ መሣሪያ ስብስብ እንኳን በደህና መጡ፤ ይህም ሙስናን ለመዋጋት አንድ ነገር ማድረግ ለመጀመር መነሳሻ ይሰጣችኋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ለሁሉም ጥያቄዎች ሁሉም መልሶች የሉንም፤ ነገር ግን በዚህ የመሳሪያ ስብስብ አማካኝነት ሙስናን የሚቃወሙ ወጣት ተሟጋቾች ማህበረሰብ ለመገንባት ተስፋ እናደርጋለን።

**YouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ ከመላው አለም እና ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ወጣቶች ቡድን ነው።**

የሥርዓተ-ፆታ እና የክልል ውክልና ለማረጋገጥ ቦርዱ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ክልሎች የተውጣጡ ሃያ ሁለት ወጣቶችን (በማመልከቻው ጊዜ ከ18 እስከ 30 ዓመት የሆናት ሴት ወይም የሆነው ወንድ ወጣት) ሲሆን ወጣቶችን የማጠንከር፣ የታማኝነት፣ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ያቀፈ ነው ፡

**መካከለኛ እስያ፣ ምስራቅ አፍሪካ፣ ምስራክ እስያ፣ አውሮፓ፣ መካከለኛ ምስራቅ፣ ሰሜን አፍሪካ፣ ሰሜን እና መካከለኛ አሜሪካ፣ ደቡባዊ አፍሪካ፣ ደቡቡ-ምስራቅ እስያ እና ፓሲፊክ፣ ደቡብ እስያ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ ምስራቅ እና መካከለኛ አፍሪካ**

## ቱልኪቱን የጻፈው ማን ነው?

እ.ኤ.አ. በ 2021 ለተካሄደው የጠቅላላ ጉባኤ ሙስና ልዩ ስብሰባ በቀጥታ አስተዋፅዖ ለማድረግ እንደ ልዩ ዝግጅት የተዘጋጀው የወጣቶች ፎረም "ሙስናን በትብብር መከላከል የወጣቶች አመለካከቶች እና ተሳትፎ" የተሰጠውን የውሳኔ ሃሳብ ተከትሎ የተባበሩት መንግስታት የአደንዛዥ ዕፅ እና ወንጀል ጽህፈት ቤት (ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ) ግሎባል ሪሶርስ ፎር አንቲ ኮራፕሽን ኤጁኬስሽን ኤንድ ዩዝ ኢምፓወርመንት (GRACE) ኢኒሼቲቭ በተባለው ክፍሉ በኩል በ 2022 የ YouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድን አቋቋመ።

የYouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ በማቋቋም የ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ አላማ ወጣቶች በ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ የፀረ-ሙስና ሥራ ላይ የሚወያዩበት እና አስተዋፅዖ የሚያደርጉበት መድረክ መስጠት እና ዓለም አቀፍ የሙስና ችግሮችን ለመቅረፍ ቀልጣፋ እና ዘላቂ መንገዶችን ለማግኘት የወጣቶችን አመለካከት ማጠናከር ነው። የቦርዱ መመስረት ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ ሙስናን ለመዋጋት ዘላቂ እና የፊቱን የሚመለከቱ ዘዴዎችን ለማግኘት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ሲሆን በዚህ ውስጥ የወጣቶች ተሳትፎ ውስጣዊ እና የማይነጠል አካል ነው።

የ2022–2024 YouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ ከ25 አገሮች የተውጣጡ 25 ወጣቶችን ያቀፈ ነው። እኛ ከአርጀንቲና፣ ብራዚል፣ ቡርኪናፋሶ፣ ቻይና፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ግብፅ፣ ኤል ሳልቫዶር፣ ጆርጂያ፣ ህንድ፣ ጣሊያን፣ ጆርዳን፣ ኬንያ፣ ሊባኖስ፣ ላይቤሪያ፣ ሞንጎሊያ፣ ኔፓል፣ ፓፑዋ ኒው ጊኒ፣ ፊሊፒንስ፣ ፖርቱጋል፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሱዳን፣ ትሪኒዳድ እና ቶቤጎ፣ ኡጋንዳ፣ ኡዝቤኪስታን እና ቬትናም ነን።



የዚህ ህትመት አዘጋጆች የYouthLED ኢንቴግሪትይ አማካሪ ቦርድ አባላይ 2022-2024

ወጣቶችን ውጤታማ እና ትርጉም ባለው የፀረ-ሙስና ጥረቶች ለማሳተፍ ስልቶችን ለዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ እንመክራለን፤ እንዲሁም ደግሞ በ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ የፀረ-ሙስና ስራ ላይ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ እንፈልጋለን። አሁን ያለው የቱልኪት ሀሳብ የተቀረፀውም በዚህ መንገድ ነው። እኛ YouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ የመጀመሪያ ቡድን እንደመሆናችን መጠን ብዙ ወጣቶች ስለ ፀረ-ሙስና ፍላጎት እንዲኖራቸው እና እውቀት እንዲያገኙ ለአጠቃቀም ቀላል የሆኑ ምክሮችን መሰብሰብ እና ማሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን እንመለከታለን።

በተ.መ.ድ. ዋና ጸሃፊ ዩዝ ኦንቮይ ጽህፈት ቤት የተጀመረው የ2022 የዳሰሳ ጥናት እንዳመለከተው “67 በመቶ የሚሆኑ ሰዎች የተሻለ የወደፊት ተስፋ እንዳለ ያምናሉ፤ ከነዚህም ከ15 እስከ 17 አመት እድሜ ያላቸው ታዳጊዎች በዚህ ላይ በጣም ብሩህ ተስፋ አላቸው። ምንም እንኳን ጉልህ መሰናክሎች ቢያጋጥሟቸውም ወጣቶች በሚያስቧቸው ጉዳዮች ላይ ድምፃቸውን ለማሰማት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ መስራታቸውን ቀጥለዋል - የወጣቶች የፖለቲካ ግድየለሽነት ተረት ነው”።[1]. በYouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ ውስጥ ለሁለት ዓመታት ከተሳተፍን በኋላ የተማርነውን ከሌሎች ወጣቶች ጋር አብሮ በመስራት እና እነሱን ለማነሳሳት እና ለማበረታታት እንደምንችል ለዚህም በታማኝነት የተሞላ የተሻለ የወደፊት እጣ ፈንታ ይኖረናል ብለን እናምናለን።

ለተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ሥራ የወጣቶች ተሟጋቾች እንደመሆናችን ብዙ ጊዜ ስራ ለመጀመር አስቸጋሪ ነበር። ብዙ ወጣቶች የድርሻቸውን እንዲወጡ፣ ብርታት እንዲሰማቸው እና የታማኝነት እሴቶችን የሚደግፍ እና ትክክል እና ስህተት የሆነውን ለማወቅ እንዲሁም ስለወደፊቱ ተስፋ እንዲሰማቸው ተጨማሪ እውቀት መጋራት እንዳለበት ተገንዝበናል። የወጣቶች ተሳትፎ የሚያሰናክልይ እንቅፋቶች መቀረፍ አለባቸውና ይህ ቱልኪት የፀረ-ሙስና ስራን ለእኩዮቻችን ተደራሽ ለማድረግ የምናደርገውን ጥረት ያመለክታል።

## ቱልኪቱ ለማን ተፃፈ?

ይህ የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭ እንዴት ማዳበር እንደሚቻል በወጣቶች ተዘጋጅቷል። ለመጀመር የሚያግዙዋችሁን አጭር እና ቀላል ምክሮችን በመስጠት የፀረ-ሙስና ተሟጋች እንድትሆኑ ለማነሳሳት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ስለ ሙስና፣ ፀረ-ሙስና፣ የወጣቶች ስራዎች እና የተባበሩት መንግስታት ስራ ትንሽ ወይም ምንም እውቀት የሌላችሁ ወጣት ከሆናችሁ እና የራሳችሁን የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭ በመገንባት በማህበረሰባችሁ፣ በክልላችሁ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ንቁ ለመሆን ፍላጎት ካላችሁ ይህ ቱልኪት ለእናንተ ነው።

አሁን ወደ ቱልኪቱ እንግባ!

[1] The Body Shop in collaboration with the Office of the Secretary-General's Envoy on Youth, “Be Seen Be Heard: Understanding young people's political participation” (2023).


# የወጣቶች የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭ ለማዳበር 10 እርምጃዎች

ከዚህ በታች የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭ ተፅዕኖ ፈጣሪ እና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ መሰረታዊ ናቸው ብለን የምናስባቸውን 10 እርምጃዎችን ለይተናል።

ይህንን መመሪያ በፈለጉት ቅደም ተከተል መጠቀም ይችላሉ። እርምጃዎቹ በጊዜ ቅደም ተከተል የተደራጁ ሲሆኑ ሁላችንም በፀረ-ሙስና ጉዟችን ውስጥ በተለያየ ደረጃ ላይ መሆናችንን እናውቃለን - ስለዚህ ለፍላጎታችሁ የሚስማማውን እርምጃ ምረጡ።

ሙሉውን ሰነድ ለማንበብ የተወሰነ ጊዜ እንድትወስዱ እንመክራችኋለን። ነገር ግን እንደፈለጉት ወደ ተለያዩ ክፍሎች ለመዝለል ነፃነት ይሰማችሁ። እርምጃ መውሰድ ለመጀመር ወደ መጨረሻው መድረስ ግዴታ አይደለም!

እነዚህ አስሩ እርምጃዎች መነሻ ናቸው፤ እንዲሁም በዚህ የመሳሪያ ስብስብ ውስጥ የተካተተው እውቀት የሙሉ በሙሉ የተምዋላ አይደለም። ነገር ግን ለመጀመር ያክል እርምጃን ለመውሰድ ለማነሳሳት ፍትሃዊና ሁሉን አቀፍ የደረጃ በደረጃ መመሪያ ነው።



# 01: እራሳችሁን አስተምሩ

በፀረ-ሙስና ንቅናቄ ውስጥ ንቁ መሆን ለመጀመር የመጀመሪያው እርምጃ ስለ ሙስና እና ሁላችንንም እንዴት እንደሚጎዳ መማር ነው። መጀመሪያ ላይ በጣም ከባድ ሆኖ ሊመስል ቢችልም በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው መረጃ የሙስናን ጽንሰ-ሀሳብ በደንብ እንድታውቁ ሊረዳችሁ እንደሚችል ተስፋ እናደርጋለን። የተለያዩ ሪሶርሶችን ከመዘርዘር ይልቅ እራሳችሁን እንዴት ማስተማር እንደምትችሉ ተከታታይ ምክሮችን ይሰጣል።

ስማርትፎን፣ ቴሌቪዥን ወይም ሬዲዮ ላይ ዜና ከተመለከታችሁ “ሙስና” ስለሚባል ነገር ታሪኮችን ወይም ቃለመጠይቆችን ሰምታችሁ ይሆናል። እነዚህ ታሪኮች በዓለም ዙሪያ ያሉ መንግስታትን፣ ተቋማትን፣ ድርጅቶችን እና የግል ኩባንያዎችን ለዓመታት ሲያናወጡ ቆይተዋል። ሙስናን በስክሪኖቻችን ወይም በጋዜጦች ወይም በከፍተኛ የመንግስት ደረጃዎች ከእኛ የራቀ ነገር አድርጎ ማሰብ አመቺ ይመስላል። ነገር ግን ሙስና ሁሉንም ሰው በቀጥታ ይነካል። ሙስና የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ በማህበረሰብ ውስጥ በጣም ተጋላጭ በሆኑ አካላት የበለጠ ያጠቃቸዋል።

ሙስና ከጥንት ጀምሮ የነበረ[2] ሲሆን በሚያሳዝን ሁኔታ ግን የትኛውም ሀገር ከሙስና ነፃ አለመሆኝ ነው።

ደረጃ በደረጃ እንሂድ…

## ሙስና ምንድን ነው?

በአሁኑ ጊዜ በጋራ ተቀባይነት ያለው የሙስና ፍቺ የለም። ስለዚህ ትርጓሜዎች ይለያያሉ። 3 ነገር ግን በሙስና ድርጊት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ሦስት አካላት አሉ ፡

(ሀ) ባለስልጣን (ኦቶሪቲ)፡ ስልጣን ያለው አንድ ሰው;

(ለ) አላግባብ ትቅም (አቢውዝ)፡ ይህ ሰው ስልጣኑን አላግባብ ሲጠቀም; እና

(ሐ) ጥቅም (ቤኔፊት)፡ ይህ ሰው ስልጣንን አላግባብ በመጠቀሙ ምክንያት የሚያገኘው ጥቅም።

ሁሉንም የሙስና ዓይነቶች የሚያብራራ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን (UNCAC) ነው።

የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን የሙስናን አጠቃላይ ፍቺ አይሰጥም። ይልቁንም በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፍ የተለያዩ የሙስና ድርጊቶችን እንደ ወንጀል ይመድባል። በተለይም ኮንቬንሽኑ ሰፊ አካሄድ እና ሰፊ ጂኦግራፊያዊ ሽፋን ያለው ሲሆን ይህም ለሙስና ምላሽ ለመስጠት ልዩ እና ሁሉን አቀፍ መሳሪያ ለማድረግ ይረዳል።

በኮንቬንሽኑ የተሸፈኑትን ልዩ የሙስና ዓይነቶች ላይ ፍላጎት ካላችሁ ይህንን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።



[2] UNODC, Knowledge tools for academics and professionals: Module Series on Anti-Corruption. Module 1: What Is Corruption and Why Should We Care? (Vienna).

| **የሙስና ዓይነቶች** | |
|---|---|
| **ጉቦ** | ጉቦ ማለት ማንኛውም አይነት ሥልጣን ያለውን አካል በመደበኛ አቅማቸው እርምጃ እንዲወስዱ ለማሳመን ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መጠየቅ ወይም መስጠት ነው። ሁለቱም የጉቦ ሂደቱ ተሳታፊዎች ህገወጥ ድርጊት እየፈጸሙ ነው። ለምሳሌ የትራፊክ ጥሰቶችን ችላ ለማለት ለፖሊስ መኮንኖች አነስተኛ መጠን ያለው ገንዘብ መክፈል፣ መረጃ ለማግኘት፣ የተለየ ህግ ለማውጣት፣ የመንግስት ኮንትራቶችን ለማስጠበቅ ወይም የግዥ ሂደቶችን ለመቆጣጠር ለፖለቲከኞች ስጦታ እና ገንዘብ መስጠት። ያስታውሱ - ተገልጋዩ ብቻ ሳይሆን ስልጣን ያለው ሰውም ጉቦ የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል! |
| **ምዝበራ** | ይህ የሙስና አይነት የሚከሰተው አንድ ዓይነት ንብረት ወይም ገንዘብ በአደራ የተሰጠው ሰው ለራሱ ለማቆየት ወይም ለሌሎች ለማስተላለፍ ሲወስን የታቀዱትን ተጠቃሚዎች በመጉዳት እና የመጀመሪያውን ዓላማ በመጣስ ነው። የተለመደው የዝርፊያ ምሳሌ አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን የህዝብ ገንዘብን ለግል ዓላማ ሲወስድ ነው። |
| **ስልጣንን አላግባብ መጠቀም** | ይህ የሙስና አይነት እንደ ደጋፊነት በመሳሰሉት ሁኔታዎች ላይ ሊተገበር ይችላል (በምርጫ ዘመቻዎች ወቅት ግለሰቦችን ለገንዘብ ድጋፍ ለመሸለም የመንግስት ሀብቶችን መጠቀም); ወገንተኝነት(ለጓደኞች እና ለዘመዶች ማዳላት); የጥቅም ትስስር/ክላዬንታሊዝም (ለምርጫ ድጋፍ ስራዎችን እና ሌሎች ጥቅሞችን መስጠት); እና ሴክሽዋል ኮራፕሽን (የወሲብ ውለታዎችን እንደ የክፍያ መጠየቅ)። |
| **አላግባብ/የማይገባ ተፅዕኖ** | ሙስና ብዙውን ጊዜ በአማላጆች (ኢንተርሚዲየሪ) ይመቻቻል። አማላጅ ማለት በአገልግሎት ሰጪዎች ወይንም በመንግስት ባለስልጣናት ላይ ያለውን ተጽእኖ ተጠቅሞ ለሌሎች ጥቅም ለማስገኘት ስልጣን ያለው ሰው ነው። እዚህ ላይ ሙስና የሚያሰኘው በአንድን ሰው ተጽእኖ ምትክ ያልተገባ ጥቅምን ማስገኘቱ ነው። |
| **ያላግባብ መበልፀግ** | አንድ የመንግስት ባለስልጣን የቅንጦት ኑሮ ሲኖር እና በመንግስት ሰራተኛው ደሞዝ ሊገዙት የማይችሉትን ንብረቶች ሲይዙ በህገ-ወጥ ማበልጸግ ጥርጣሬ አለ። ይህ በግሉ ዘርፍ ውስጥ ለሚሰሩ ሰዎችም ሊተገበር ይችላል። |
| **ሌሎች ተዛማጅ ወንጀሎች** | ሙስና ብዙውን ጊዜ እንደ ማጭበርበር እና ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ካሉ ኢኮኖሚያዊ ወንጀሎች ጋር የተቆራኘ ቢሆንም ሁሉም የተለያዩ ወንጀሎች መሆናቸውን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ሁሉም የገንዘብ ማጭበርበር (ፍሮድ) ሙስና አይደለም፤ ኢንዲሁም ሁሉም የሙስና ድርጊት የገንዘብ ማጭበርበርን የሚያካትት አይደለም። |
| **ማጭበርበር (ፍሮድ)** | ይህ የሚያመለክተው አንዳንድ ዓይነት ማጭበርበር እና ስርቆትን የሚያካትት ሰፋ ያለ የወንጀል ምድብ ነው። አንዳንድ የሙስና ዓይነቶች በዚህ ምድብ ውስጥ ቢወድቁም ከላይ የተገለፀውን የሙስና አካል የሌላቸው ሌሎች የማጭበርበር ዓይነቶችም አሉ። ለምሳሌ የግብር ማጭበርበር ወይም የፋይናንስ ሰነዶችን እና መረጃዎችን ማጭበርበር የመንግስት ባለስልጣናት ወይም የግሉ ሴክተር ሰራተኛ እርዳታ ሳይኖር ሊከሰት ይችላል። ስለዚህ እነዚህን ወንጀሎች ለመፈጸም አንድ ሰው ጉቦ መስጠት አያስፈልግም። |

**ይህን ያውቁ ኖሯል...** የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን ሙስናን ለመከላከል እና ለመዋጋት ብቸኛው ዓለም አቀፍ የሕግ አስገዳጅ ማዕቀፍ ነው። እ.ኤ.አ. በ 2003 የፀደቀው ከ 190 የሀገራት መንግስታት ጋር በአለም አቀፍ ደረጃ ከሞላ ጎደል ተግባራዊ ሆኗል። እና ይህ ቁጥር በመጨመር ላይ ይገኛል!

የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽኑ አስፈጻሚ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ ሲሆን በሙስና ጉዳይ ላይ የተለያዩ ግብዓቶችን ይሰጣል።

ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ ሙስናን በመከላከል ረገድ የትምህርት እና የወጣቶችን ማጎልበት ሚና ለማሳደግ እና ለተለያዩ ትኩረት የተሰጠባቸው ቡድኖች (አስተማሪዎች፣ ምሁራን፣ ወጣቶች እና ልጆች) ግሎባል ሪሶርስ ፎር አንቲ ኮራፕሽን ኤጁኬሽን ኤንድ ዩዝ ኢምፓወርመንት (GRACE) ኢኒሼቲቭን ጀምሯል። የ GRACE ኢኒሼቲቭ አላማ የትምህርት እና የወጣቶችን ማጎልበት ሃይል በመጠቀም በልጆች እና በወጣቶች መካከል ሙስናን የመቃወም ባህል መፍጠር ነው። የ GRACE ድህረ ገጽን በመጎብኘት ስለዚህ ርዕስ ተደራሽ በሆነ መንገድ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ። ልዩ ትኩረት የሚሰቡ እና ሙስናን እና የተለያዩ ልኬቶቹን ለመረዳት አጋዥ የሆኑት ፀረ-ሙስና፣ ታማኝነት እና የሥነ-ምግባር ትምህርትን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለማጠናከር የተገነቡ የተለያዩ ሞጁሎች እና ለወጣቶች የተዘጋጁ መሳሪያዎች ይገኙበታል። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ :

- ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ, "University Module Series on Anti-Corruption"
- ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ, "University Module Series on Integrity and Ethics"
- ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ, "Youth Anti-Corruption Tools and Events"

የትምህርት ጉዟችሁን ሊደግፉ የሚችሉ ሌሎች በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸው ህጎች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም አሉ። በርካታ ዓለም አቀፍ እና ባለብዙ ወገን ድርጅቶች ብሄራዊ የፀረ-ሙስና ጥረቶችን ለመምራት እና ለማሳደግ የጋራ ማዕቀፎችን አቋቁመዋል። እነዚህ ማዕቀፎች ሙስናን የሚገልጹ የፀረ-ሙስና ሂደቶችን የሚቆጣጠሩ እና በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ ታማኝነትን የሚያበረታቱ ህጎችን፣ ደንቦችን፣ እና ሪሶርሶችን ያቀፈ ነው። በስምምነቶች አማካኝነት ድንበር ተሻጋሪ ሙስናን ለመዋጋት ፖሊሲዎችን ለማሻሻል እና በአገሮች መካከል ትብብርን ለማመቻቸት መንግስታት እንደ ዋቢ ሆነው ያገለግላሉ።

| ዓለም አቀፍ ድርጅት | ሕግ ማውጣት |
|---|---|
| **የአሜሪካ መንግስታት ድርጅት** | ኢንተር አሜሪካ የፀረ ሙስና ስምምነት |
| **የአውሮፓ ህብረት ምክር ቤት** | የአውሮፓ ማህበረሰቦች ባለስልጣናት ወይም የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ባለስልጣናት ላይ የሚደርሰውን ሙስና ለመዋጋት ስምምነት<br><br>የሙስና ወንጀል ሕግ ስምምነት |
| **የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት** | በአለም አቀፍ የንግድ ልውውጦች ውስጥ የውጭ የመንግስት ባለስልጣናትን ጉቦ የመዋጋት ስምምነት |
| **የአፍሪካ ህብረት** | የአፍሪካ ህብረት ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ስምምነት |
| **የአረብ ሊግ** | የአረብ ፀረ-ሙስና ስምምነት |

አንዳንድ ጊዜ ከሥነ ምግባር አኳያ የላቀ ምርጫዎች የማይገኙ፣ ጉድለት ያለባቸው ወይም በጣም ውድ እንደሆኑ ሲታሰቡ ሙስና በተወሰኑ አካባቢዎች "ጉዳዮችን ለማስፈጸም" ምርጡ መንገድ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ ለታማኝነት ባህል እና ለፀረ-ሙስናለ ስንሟገት ችላ ሊባል የማይገባው እውነታ ነው። ይህ የግንዛቤ ብዛት ሙስና ዘርፈ ብዙ ጽንሰ-ሐሳብ መሆኑን ይጠቁማል። በተፈጥሮ፣ በተለያዩ አውዶች ውስጥ በተለያዩ ተዋናዮች የተለያዩ ድርጊቶችን ይሸፍናል። ስለ ሙስና የተለያዩ ግንዛቤዎች እንዳሉ መቀበል እና ወደዚህ የመረዳት ፈተና መነሳት ስለ ችግሩ የተቀናጀ እና ሁለገብ ግንዛቤን እና ችግሩን ለመፍታት መንገዶችን ለማዳበር ይረዳናል።

ከፀረ-ሙስና አስተሳሰብ በስተጀርባ ያሉት እሴቶች ታማኝነት እና ትክክል እና ስህተት የሆነውን ግልጽ መረዳት ነው። ታማኝነት እና ሥነ ምግባራዊ ባህሪ መኖር ማለት በህግ እና በብሔራዊ የፖሊሲ ማዕቀፎች መሰረት መስራት ብቻ ሳይሆን ማንም በማይመለከትበት ጊዜም እንኳ ትክክለኛውን ነገር በማድረግ ከዚህ አልፈው መሄድ ማለት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ አንዳንድ ድርጊቶች ህጋዊ እንጂ ሥነ ምግባራዊ እንዳልሆኑ ልንመለከት እንችላለን፤ ሌሎች ደግሞ ሥነ-ምግባራዊ እንጂ ህጋዊ አይደሉም።

[3] See the "What is corruption?" page of the website of the UNODC Corruption and Economic Crime Branch, available at www.unodc.org/corruption/en/learn/index.html.

[4] UNODC, "Knowledge tools for academics and professionals: Module Series on Integrity and Ethics. Module 12: Integrity, Ethics and Law" (Vienna).

ታማኝነትን መኖር ማለት ሙስና የተለመደ መሆን እንደሌለበት መገንዘብ እና ታማኝነትን መላበል እና ሥነ ምግባራዊ ባህሪ ማለት ደግሞ በጎ ሥነ ምግባር ምን ማለት እንደሆነ መገንዘብና መኖር አንዳንዴም ከህግ በላይ መሄድ ማለት መሆኑን መረዳት ማለት ነው። የ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ በሥነ ምግባር፣ በታማኝነት እና በህግ ላይ የተዘጋጁትን ሞጁሎች እንዲመለከቱ[4] እና በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ ውስጥ በታማኝነት እና በበጎ ሥነ ምግባር እንዴት መኖር እንደሚቻል ለመረዳት እንዲያነብዋቸው እናበረታታችኋለን።

አሁን ለታማኝነት ባህል የሚያስፈልጉትን ዋና እሴቶች ከተረዱ እና ሙስና ምን እንደሆነ እንዲሁም እሱን ለመከላከል እና ለመከላከል ምን ዓይነት ብሔራዊ እና አለምአቀፍ ዘዴዎች እንዳሉ የተሻለ ግንዛቤ ካላችሁ በአገራችሁ ያለውን አውድ መመልከት ይፈልጉ ይሆናል።

ማድረግ ያለባችሁ የመጀመሪያው ነገር ሙስና፣ አስተዳደር እና ሌሎች ሊፈልጓቸው የሚችሏቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ በአገራችሁ ያለውን ሁኔታ መመርመር ነው።

በአገራችሁ ውስጥ በሙስና፣ በታማኝነት እና በሥነ-ምግባር ላይ ያሉትን ህጎች መመልከት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም እነዚህ እናንተን የሚመሩእና የአካባቢያችሁ ባለስልጣናት እና ብሄራዊ መንግስት እንዴት እንደሚሰሩ የሚቆጣጠሩ ህጎች ናቸው። ለፀረ-ሙስና ማዕቀፍ እድገት አስተዋፅዖ የሚያደርጉትን ሰፊ የሕጎች እንዴት መረዳት እንደሚችሉ ለመምራት ከዚህ በታች የጥያቄዎችን ስብስብ አዘጋጅተናል -

በአገራችሁ ያለውን የህግ እና የፖሊሲ ስርዓት ጥንካሬ የበለጠ ለመረዳት ጥሩ መነሻ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን አፈፃፀም ግምገማ ዘዴን መመልከት ነው። በ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ በተቀናጀው በዚህ የአቻ ግምገማ ሂደት የኮንቬንሽኑን የትግበራ ደረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ መገምገም ይችላሉ።[5]

---

## በአገራችሁ ውስጥ የፀረ-ሙስና ማዕቀፍ ምን እንደሚመስል እንዴት ማወቅ እንደሚቻል

| | | |
|---|---|---|
| 1 | መንግስት የፀረ-ሙስና ስትራቴጂ አለው ወይ? | ○ አዎ ○ አይ |
| 2 | መንግስታችሁ የፀረ-ሙስና ህግ አለው? | ○ አዎ ○ አይ |
| 3 | መንግስት የመረጃ ነፃነት ህግ አለው? | □ አዎ □ አይ |
| 4 | መንግስት ሙስናን የሚያጋልጡ ሰዎችን ወይም ዊስል ብሎወሮችን የሚጠብቅ ህግ አለው? | □ አዎ □ አይ |
| 5 | በአገራችሁ ህጎች ውስጥ ታማኝነት ምን ጉዳይ ላይ ተጠቅሷል? | |
| | • የፍትህ ታማኝነት እና የፍትህ ስርዓቱ ነፃነት ላይ ተጠቅሷል? | ○ አዎ ○ አይ |
| | • ለመንግስት ሰራተኞች የሥነ-ምግባር ደንብ (ኮድ ኦፍ ኮንዳክት) አለ? | ○ አዎ ○ አይ |
| | • ለመምህራን እና ለፕሮፌሰሮች የሥነ-ምግባር ደንብ (ኮድ ኦፍ እቲክስ/ኮንዳክት) አለ? | □ አዎ □ አይ |
| 6 | ከሙስና፣ ከታማኝነት እና ከሥነ ምግባር ጋር በተያያዘ የግል ንግዶች ባህሪ በአገራችሁ ውስጥ ባለው ፖሊሲ እና የህግ ስርዓት ውስጥ በየትኛውም ቦታ ተጠቅሷል? | □ አዎ □ አይ |
| | • በአገራችሁ ውስጥ የንግድ ድርጅቶች ታማኝነት ቁጥጥር ይደረግበታል? | ○ አዎ ○ አይ |

# 02: ትኩረት የምታረጉበትን ጉዳይ ምረጡ

አሁን ስለ ርዕሱ የተወሰነ እውቀት ስላዳበርን ትኩረት እንድትመርጡ እንመክራችኋለን። ይህ ኢኒሼቲቫችሁን ትኩረት/አድማስ ለማጥበብ ይረዳችኋል፤ ይህም የበለጠ ተፅዕኖ እንዲኖረው ያደርገዋል። ይህንን ለማድረግ እንዲረዳችሁ ሙስና በብዙ ዘርፎች እና አካባቢዎች ላይ እንዴት እንደሚጎዳ ከዚህ በታች መማር ትችላላችሁ። ይህ የተሟላ ዝርዝር እንዳልሆነ ሊናሳስብ ኢንወዳለን፤ ነገር ግን ግንኙነቶችን መፍጠርን በተመለከተ መነሻ ነጥብ ለእናንተ ለማቅረብ የተነደፈ ነው። እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች የተመረጡት በእኛ YouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ አባላት ነው፤ ምክንያቱም ለወጣቶች እና ለፀረ-ሙስና አጀንዳ ጠቃሚ እንደሆኑ እንቆጥረዋለን።

## ሙስና እና ሰብአዊ መብቶች

የጤና እንክብካቤ፣ የትምህርት እና የንፁህ ውሃ ተደራሽነት እንዲሁም በፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የመሳተፍ ዕድል በሙስና ድርጊቶች ለምሳሌ በጉቦ እና በምዝበራ ሊገደብ ይችላል።[6] ሙስና ለሰብአዊ መብቶች ሁሉ እንቅፋት ነው። ሙስና ተቋማትን በሚያዳክምበት ጊዜ ሀገራት የሰብአዊ መብት ማዕቀፎችን በበቂ ሁኔታ መገንባትና መተግበር ሊያስቸግራቸው ይችላል።

በፀረ-ሙስና ጥረቶች እና በሰብአዊ መብቶች ጥበቃ መካከል ያለውን አዎንታዊ ግንኙነትም ልብ ሊባል ይገባል። ሙስናን ለመከላከል እና ለመዋጋት እርምጃ መውሰድ የሰብአዊ መብቶች በተሻለ ሁኔታ የሚጠበቁበት፣ የሚከበሩበት እና የሚስተዋወቁበት አካባቢ ለመፍጠር ይረዳል። በተቃራኒው የሰብአዊ መብቶችን ማስከበር የፀረ-ሙስና ጥረቶችን ሊረዳ ይችላል።

እ.ኤ.አ. በ2021 ሙስናን አስመልክቶ ጠቅላላ ጉባኤ ባካሄደው ልዩ ስብሰባ ላይ ባፀደቀው "ተግዳሮቶችን በብቃት ለመቅረፍ፣ ሙስናን ለመከላከል እና ለመዋጋት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማጠናከር እርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የጋራ ቁርጠኝነት" በሚል ርዕስ በወጣው የፖለቲካ መግለጫ አባል ሀገራት ማንኛውም ዓይነት ሙስና መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማግኘት እና ሁሉንም ሰብአዊ መብቶች መጠቀም ላይ ሊያደርስ ስለሚችለው አሉታዊ ተፅእኖ ስጋታቸውን ገልጸዋል። ይህም ድህነትን እና ኢ-እኩልነትን ሊያባብስ እና በህብረተሰቡ ውስጥ በጣም የተጎዱ ግለሰቦችን ባልተመጣጠነ መልኩ ሊጎዳ እንደሚችል በመገንዘብ ሙስናን ለመከላከል እና ለመዋጋት እንዲሁም በሰብአዊ መብቶች፣ በፍትህ፣ በዴሞክራሲ እና በሕግ የበላይነት ላይ ባላቸው ግዴታዎች መሠረት በሁሉም ደረጃዎች ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማጠናከር ቃል ገብተዋል።

> **‹‹ሙስና ባለበት ሰብአዊ መብቶች ይጠፋሉ››**
>
> - ኦላጀቢ ማኪንዋ፣ ኃላፊ፣ አፍሪካ፣ የተባበሩት መንግስታት ግሎባል ኮምፓክት

የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ባወጣው ውሳኔ 21/13 የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት ከየካቲት 25 እስከ መጋቢት 22 ቀን 2013 በተካሄደው ሃያ ሁለተኛ ስብሰባ ላይ ሙስና በሰብአዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅእኖ በሚመለከት የፓናል ውይይት እንዲያዘጋጅ ጠይቋል።




በውይይቱ ወቅት የተደረሱት መደምደሚያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ :

- ሙስና ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ አድልዎ የሌለበት እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ (meaningful engagement) መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች መርሆዎችን ይጥሳል።
- ሙስና እንደ ሴቶች እና ህጻናት ላሉ ተጋላጭ ለሆኑ ቡድኖች በተለይም በገጠር ወይም በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን እና ሰብአዊ መብቶችን ማግኘት እንቅፋት ሆኗል። በእኩልነት እና በመስቀለኛ መንገድ መድልዎ [7] ምክንያት ሙስና በሴቶች፣ ህጻናት፣ ስደተኞች፣ አካል ጉዳተኞች እና በድህነት ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች ላይ የከፋ ተጽእኖ ይኖረዋል ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ በሕዝብ እቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ ጥገኛ ስለሆኑ እና አማራጭ የግል አገልግሎቶችን ለመፈለግ የሚያስችል አቅም ውስን ነው።
- ሙስና በተለይ ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች የፍትህ ተደራሽነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል።
- ሙስና ሰዎች በሕዝብ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ዲዛይን እና ትግበራ ላይ የመሳተፍ እድላቸውን ይገድባል እና ሰዎች ተጠያቂነትን እና ካሳ እንዲፈልጉ የሚያደርገውን ሃብት ያሳጣቸዋል።

[5] See the Implementation Review Mechanism page on the website of the United Nations Office on Drugs and Crime, available at www.unodc.org/

[6] UNODC, "Knowledge tools for academics and professionals: Module Series on Anti-Corruption. Module 7: Corruption and Human Rights" (Vienna).

[16] Transparency International, "Breaking the Silence Around Sextortion: The links between power, sex and corruption" (2020).

እ.ኤ.አ. በሐምሌ 2021 የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ሙስና በሰብአዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእኖ በተመለከተ ውሳኔ 47/7 አጽድቋል። በዚህ ውሳኔ ላይ ምክር ቤቱ ሙስናን በመከላከል ረገድ ስላሉት ተግዳሮቶች እና መልካም ልምዶች እንዲሁም ሙስና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ አውድ ውስጥ በሰብአዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ ስላሳደረው ተጽእኖ በክፍለ-ጊዜያት መካከል ፓናል ውይይት ለማካሄድ ወስኗል። ፓናሉ የተካሄደው በየካቲት 15 ቀን 2022 ነው።

የፀረ-ሙስና ጥረቶች እና የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ እርስ በርስ የሚደጋገፉ መሆናቸው በሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ሙስና በሰብአዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ ስለሚያስከትለው አሉታዊ ተፅእኖ በተመለከተው ውሳኔ 47/7 ላይ እውቅና ተሰጥቶታል። በዚህ ውሳኔ ምክር ቤቱ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት እና ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ በሙስና እና በሰብአዊ መብቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ግንዛቤ ለማጠናከር ሃሳብ እንዲለዋወጡ ጋብዟል።

የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ህገወጥ ምንጭ ያለው ገንዘብ ወደ መጡበት ሀገራት ባለመመለሱ በሰብአዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ ስለሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ በተመለከተው ውሳኔ 52/21 ላይ የተባበሩት መንግስታት የሙስና ኮንቬንሽን አባል ሀገራት ጉባኤ ሰብአዊ መብቶችን ሙሉ በሙሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት ኮንቬንሽኑን ተግባራዊ የሚያደርጉበትን መንገዶች እንዲያጤን ጋብዟል።

በዚህ ክፍል ውስጥ ተጨማሪ ሰብአዊ መብቶችን እና ከሙስና ጋር ያላቸውን ግንኙነት የምንዳስስ ቢሆንም በሁለቱ መካከል ስላለው ግንኙነት እንዲሁም ሙስና በግለሰብ ሰብአዊ መብቶች ላይ ስላለው ተጽእኖ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ "የፀረ-ሙስና ሞዱል ሲሪስ - ሞጁል 7 ሙስና እና ሰብአዊ መብቶች"ን ይመልከቱ።

እ.ኤ.አ. በ2019 በኖርዌይ የሚገኝ አንድ የክልል ገዥ ሥልጣኑን አላግባብ በመጠቀም እና ሦስት ወጣት ወንድ የጥገኝነት ጠያቂዎችን (ከእነሱም አንዱ 17 ዓመት ዕድሜ ነበር) ተጋላጭነት በመጠቀም ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

ሦስቱ ግለሰቦች ለገዥው የጾታ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ከአገር እንዲባረሩ ወይም ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኙ ሊያደርግ እንደሚችል እንደሚያስቡ ገልጸዋል።[17]



**የኢንተሴክሽናል አድልዎ ፍቺ**

እንደ አውሮፓ ምክር ቤት ገለጻ የኢንተሴክሽናል አድልዎ የሚከሰተው ሁለት ወይም ከዛ በላይ ምክንያቶች በአንድ ጊዜ ሲከሰቱ እና እነዚህም ማይነጣጠሉ ሲሆኑ ይህም የተለያዩ እና የተወሰኑ የመድልዎ ዓይነቶችን ይፈጥራል።

የብዙ መድልዎ ጽንሰ-ሀሳብ መድልዎ ከአንድ በላይ በሚታዩ ባህሪያት ላይ የተመሠረተ ሊሆን እንደሚችል ይገነዘባል።

ለምሳሌ በጎሳው ምክንያት መድልዎ የተደረገበት ሰው በጾታ፣ በጾታዊ ዝንባሌ ወይም በእድሜ ወዘተ ምክንያት መድልዎ ሊደርስበት ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ መድልዎ ድምር ጉዳት ሊፈጥር ይችላል እና ብዙ ጊዜም ይከሰታል።

በ1995 በዓለም አቀፍ የሴቶች ኮንፈረንስ ላይ እድሜ፣ አካል ጉዳት፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ጎሳ እና ዘር ለሴቶች ልዩ እንቅፋቶችን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ትኩረት ተሰጥቷል።

ይህም የቤጂንግ ፕላትፎርም ፎር አክሽን አካል የሆነው በርካታ እና አብረው የሚኖሩ የመድልዎ ዓይነቶችን ለመለየት የሚያስችል ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ምክንያት ሆኗል።

## ሙስና በትምህርት ዘርፍ

ትምህርት ለሙያዊ፣ ለግል እና ለማህበራዊ እድገት ዋና ዋልታ፣ መሰረታዊ ሰብአዊ መብት እና ሌሎች በርካታ መብቶችን እንዲሁም ነፃነቶችን ለማስጠበቅም መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ ነው። አስፈላጊነቱን በመገንዘብ በ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳ ላይ ሁሉን አቀፍ እና ፍትሃዊ ጥራት ያለው ትምህርትን ለማረጋገጥ እና ለሁሉም የዕድሜ ልክ የመማር እድልን ለማዳረስ የጋራ ጥረት መደረግ እንዳለበት ተገልጽዋል (ዘላቂ ልማት ግብ 4)።

ሙስና የትምህርትን እኩል ተደራሽነት በእጅጉ አደጋ ላይ በመጣል እና የትምህርትን ጥራት በማበላሸት ይህን ግብ ለማሳካት ካሉት ዋና ዋና እንቅፋቶች አንዱ ነው። ስለዚህ በትምህርት ዘርፍ የተለያዩ የሙስና ድርጊቶችን መለየት መቻል እና ጎጂ ውጤቶቻቸውን ማወቅ ከሙስና ነፃ የሆነ ትምህርት ስላለው አስፈላጊነት ግንዛቤ ለማሳደግ ወሳኝ ነው። ስለዚህ የወጣቶችን እና ሌሎች የትምህርት ማህበረሰብ አባላትን ማጎልበት እና አቅማቸውን መገንባት በዚህ ዘርፍ እና ከዚያም በላይ የፀረ-ሙስና ስልቶችን ለማዘጋጀት ያስችላል።

[7] Intersectional discrimination recognized by the 1995 World Conference for Women

[8] UNODC, "Knowledge tools for academics and professionals: Module Series on Anti-Corruption. Module 9: Corruption in Education" (Vienna).

[17] BBC, "Norway ex-minister Svein Ludvigsen guilty of sexually abusing asylum seekers", 5 July 2019.

[9] Committee on Economic, Social and Cultural Rights, general comment No. 13 (1999) on the right to education.

ነገር ግን በትምህርት ውስጥ ሙስና ከየት ሊመነጭ ይችላል? ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ያለምንም ጥርጥር "ሄርኩሊያን ታስክ" ነው። ሆኖም በትምህርት ዘርፍ የሙስና ድርጊቶች እንዲስፋፉ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፦

(ሀ) ከፍተኛ ምላሽን/ጥቅምን መጠበቅ - ሰዎች የትምህርት ማዕረጋቸውን ተጠቅመው ምቹ ኑሮ ለመኖር እና/ወይም ጥሩ ደመወዝ ያለው ሥራ ለማግኘት ተስፋ ያደርጋሉ፤ በዚህም ምክንያት መደበኛ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ወይም ውጤታቸውን ለማሻሻል ጉቦ ለመክፈል ወይም በሌሎች የሙስና ድርጊቶች ውስጥ ለመሳተፍ በጣም የተጋለጡ ናቸው፤ እና

(ለ) የመንግስት ባለስልጣናትና አስተማሪዎች ዝቅተኛ ደመወዝ፣ የትምህርት ተቋማት የገንዘብ እጥረት፣ እና በብዙ አገሮች የትምህርት መሠረተ ልማት እጥረትን ያካትታሉ[8]። ሌሎች ሊጠቀሱ የሚገባቸው ምክንያቶች ደግሞ የቁጥጥር እና የመመዘኛ እጥረት፣ በቂ ያልሆኑ ድርጅታዊ መዋቅሮች መኖር እና ትርጉም ያለው የማህበረሰብ ተሳትፎ ቻናሎች አለመኖር ናቸው[9]።

በተጨማሪም የህግ ማዕቀፍ ብዙ ጊዜ ቢኖርም ደካማ ወይም በቂ ያልሆኑ የህግ አስከባሪ አካላት እንዲሁም ህጎችን የመቆጣጠርና የማስፈጸም ደካማ ተቋማዊ አቅም አሁንም ትልቅ ፈተና ሆኖ ይቀጥላል።

በአጠቃላይ ሙስና በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አለው። በትምህርት ውስጥ ሙስና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተፅእኖ አለው። ይህም ወዲያውኑ እና በረጅም ጊዜ ውስጥ ሊታይ ይችላል። ለምሳሌ የብልሹ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች ገና በለጋ ዕድሜያቸው የማጭበርበር ድርጊቶችን የመፈጸም ልማድ እንዲያዳብሩ በማድረግ እና ሜሪቶክራሲን በገንዘብ በመቀየር ለሙስና መስፋፊያ ሆነው ያገለግላሉ። ከዚህም በላይ በትምህርት ዘርፍ ያለው ሙስና ለማህበራዊ መተማመን መሸርሸር አስተዋፅኦ ያደርጋል፤ እንዲሁም የተማሩ፣ ብቁ እና ሥነ-ምግባር ያላቸው ዜጎችና መሪዎች እንዳይፈጠሩ በማደናቀፍ እድገትን ያበላሻል[10]። እንዲሁም በሰብአዊ መብቶች ክፍል ላይ እንደተገለፀው የሙስና መዘዝ በተለይ በኑሮ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉና ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች የበለጠ ከባድ ይሆናል፤ የመማር አቅም ስለሌላቸው ከድህነት እና ከመገለል ለማምለጥ ያላቸው ዕድል አነስተኛ ነው።[11] ስለዚህ የሙስና ድርጊቶች ይህ ልማድ እንዲደጋገምና ኢ-እኩልነት እንዲባባስ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፣ ማህበራዊ እንቅስቃሴን ያደናቅፋሉ እንዲሁም ህብረተሰቡ እንዳይሻሻል እና እንዳያብብ ያግዳሉ።

## የሙስና ምሳሌዎች በትምህርት ዘርፍ ያሉ ምሳሌዎች

| መዋቅራዊ ሙስና በትምህርት ዘርፍ | የግለሰብ ሙስና በትምህርት ዘርፍ |
|---|---|
| በሙስና ምክንያት የጠፋው ገንዘብ በትምህርት ዘርፍ ኢንቨስት አይደረግም | ተቋማዊ ጥቅሞችን ለማግኘት ሲባል ዲግሪዎችን አግባቡ ባልሆነ መንገድ ማግኘት |
| የመምህራን ምልመላ በዘመድ አዝማድ፣ አድልዎ፣ በጥቅም ግጭት፣ ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም እና ጉቦ፣ ወሲባዊ ጉቦን ጨምሮ በመስጠት ተጽዕኖ ያሳድራል<br>የማስተማር ጥራት በመቀነስ እንዲሁም ልጆች በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸውን የትምህርት ግቦች ሳያምዋሉ ይቀራሉ | የማለፊያ ነጥቦችን በተለያዩ ውለታዎች (ጉቦ ክፍያ፣ ወሲባዊ ሙስና፣ ወዘተ) መስጠት |
| በግዥ ላይ የሚደርሰው ሙስና፣ ገንዘብ ማዘረፍ እና ገንዘብ ማዛወር የትምህርት ተቋማትን በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ሀብቶች እና አቅርቦቶች ያሳጣቸዋል | ነፃ ለሆኑ የትምህርት አገልግሎቶች ጉቦ እና የማጭበርበር "ክፍያዎች" መክፈል |

10 Transparency International, "Corruption in the Education Sector: An Introduction" (2004).

11 Monica Kirya, "Education sector corruption: How to assess it and ways to address it", U4, vol. 5 (2019).

## ሙስና እና ሥርዓተ-ፆታ

ሙስና እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት በብዙ መንገዶች በቅርበት የተሳሰሩ ጉዳዮች ናቸው። በተለምዶ ሴቶች በሙስና ውስጥ የሚሳተፉባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት በመሆናቸው ሙስና ከሴቶች ጋር ያልተያያዘ ጉዳይ እንደሆነ ይታሰባል። ይሁን እንጂ ከማህበረሰባችን የሥርዓተ-ፆታ መዋቅሮች ጋር በተያያዘ የኃይል ልዩነቶችን በጥልቀት የመረመሩ ጥናቶች ይህንን ጽንሰ-ሐሳብ ውድቅ አድርገዋል። ሴቶች ከወንዶች ያነሰ የሙስና ተሳትፎ ያላቸው መሆናቸው በተፈጥሮ የተለዩ ስለሆኑ ሳይሆን በታሪክ አውድ ውስጥ በፓትሪያርካል ማህበረሰቦች ውስጥ የነበራቸው የተገደበ ኃይል ምክንያት ነው።[12]

ከዚህ በተጨማሪ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማሳደግ በተለምዶ በወንዶች የሚበረታቱ እና ከሴቶች ይልቅ ወንዶችን የሚጠቅሙ የትብብር ኔትወርኮችን ሊያስተጓጉል ይችላል። በርካታ ጥናቶችም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማጠናከር እና የሴቶችን ውክልና ማሳደግ በተቋማት ውስጥ ግልጽነትን እንደሚያጠናክር እና በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና በፀረ-ሙስና ጥረቶች መካከል እርስ በርስ የሚደጋገፍ ግንኙነት እንዳለ ያመለክታሉ።

በአጠቃላይ ሴቶች በእኩልነት እጦት እና በሥርዓተ-ፆታ ላይ በተመሰረተ የሥልጣን ግንኙነት ምክንያት ሙስናን እና ውጤቶቹን በተለያየ መንገድ ይጋፈጣሉ። የተለመዱ መገለጫዎች ሴቶችን የህዝብ ሀብት፣ መረጃ እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ያላቸውን ተደራሽነት መገደብን ያካትታሉ። ይህም ማህበራዊ ደንቦችን፣ ባህላዊ አመለካከቶችን እና የፖለቲካ ተጽዕኖዎችን የበለጠ ሊያጠናክር ይችላል።

በተጨማሪም ሙስና በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን አድልዎ በማንፀባረቅ በሴቶች ላይ ያልተመጣጠነ ተጽዕኖ ያሳድራል። ለምሳሌ ወሲባዊ ድርጊቶች በሙስና ውስጥ እንደ ምንዛሬ ("ወሲባዊ ሙስና") ጥቅም ላይ እንደሚውሉ የሚያሳዩ ማስረጃዎች አሉ። በእነዚህ ሁኔታዎች አንድ ሰው ተጋላጭ የሆነን ግለሰብ (ብዙ ጊዜ ሴት ወይም ሴት ልጅ) በነጻ ሊያገኝ የሚገባውን አገልግሎት ለማግኘት ሲል ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲፈጽም ያስገድዳል ወይም ይጠይቃል።[13] እንደ አለመታደል ሆኖ እነዚህ ሁኔታዎች ሁልጊዜ በሕግ እንደ ሙስና ወንጀሎች አይታወቁም። ይህም በተጠቂዎች ላይ በሚደርስ ማሸማቀቅ እና ተጎጂዎችን የመወንጀል ባህል ምክንያት ክስተቶቹ ሪፖርት እንዳይደረጉ ሊያደርግ ይችላል። እንዲሁም ሙስና በLGBTQI+ ማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ ሲያሳድር በአንዳንድ አውዶች ተመሳሳይ ጾታ ግንኙነቶችን ሕገ-ወጥ የሚያደርጉ ሕጎች ምክንያት ተጽዕኖው የበለጠ ሊደበቅ ይችላል።

በዚህ ርዕስ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲን በሙስና እና በሥርዓተ-ፆታ ላይ ያተኮረ ሞጁል[14] The Time is Now: Addressing the Gender Dimensions of Corruption.

እ.ኤ.አ. በሰኔ 2009 በአውስትራሊያ የሚገኘው የሙስና እና ወንጀል ኮሚሽን አንድ ምሁር በሚያስተምሩበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ለመስጠት ሴት ተማሪዎች የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ጫና አድርጓል በሚል ክስ ላይ ምርመራ ከፈተ።



ምርመራው በሙስና እና ወንጀል ኮሚሽን ሕግ መሠረት ምሁሩ ከሴት የውጭ ተማሪዎች የጾታ ውለታ በመጠየቅ ለግል ጥቅሙ ለማዋል ሥልጣኑን በመጠቀም ከባድ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሟል በሚል ውሳኔ ላይ ደርሷል።[15]




[12] UNODC, "Knowledge tools for academics and professionals: Module Series on Anti-Corruption. Module 8: Corruption and Gender" (Vienna).

[13] UNODC, The Time is Now: Addressing the Gender Dimensions of Corruption (Vienna, 2020).

[14] UNODC, "Knowledge tools for academics and professionals: Module Series on Anti-Corruption. Module 8: Corruption and Gender" (Vienna).

[15] Corruption and Crime Commission of Australia, Report on the Investigation of Alleged Public Sector Misconduct by Dr Nasrul Ameer Ali as a sessional academic employed by Curtin University of Technology (September 2010).




**በነዚህ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል:**

**ሙስና የሴቶችን እድሎች ይቀንሳል**

**በስልጣን ላይ ያሉ ሴቶች ሙስናን ይቀንሳሉ**

**ለዚህ ምክንያት ምናልባት:**

- የሴቶች ኢ-እኩልነት አነስተኛ ኃይል ባላቸው ሴቶች ላይ ከሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽእኖዎች በተጨማሪ በጉቦ ፋንታ ጾታዊ ሙስና ዓይነቶችን መጠቀም ጉዳቶችን የበለጠ ይባባሳል።
- ሴቶች በሙስና ስርዓቶች ውስጥ ያሉ የመንግስት ባለስልጣናትን በአነስተኛ ኃይል ባላቸው ሰዎችን ላይ በአድልዎ እንደሚፈጽሙ ያምናሉ። ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ከፍ ባለ የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዳላችው እንደሚታመን ያስባልይ። በዚህም ምክንያት ሴቶች ተጨማሪ ሥልጣን ቢፈልጉ ኢ-ፍትሃዊ አያያዝ እንደሚገጥማቸው ያስባሉ፤ ስለዚህም ከመሞከር ይቆጠባሉ።
- በወንዶች የሚተዳደሩ ብልሹ ተግባራትን የሚያከናውኑ እና የስልጣን ተደራሽነትን የሚቆጣጠሩ ኔትወርኮች ሴቶችን ያገላሉ፤ በዚህም የማስኪውሊን ደንቦችን በመጠቀም በተለያዩ መንገዶች ከመሳተፍ ያስቀሯቸዋል

- የሙያ እድገት እድሎችን ለማሻሻል በስልጣን ላይ ያሉ ሴቶች በወንዶች በሚተዳደሩ አውታረ መረቦችንና የተቀናጁ የሙስና ድርጊቶችን ይቋረጣሉ።
- በስልጣን ላይ ያሉ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ለንፁህ አስተዳደር ጠንካራ ማበረታቻዎች ስለሚያጋጥሟቸው ሙስናን ያስወግዳሉ። ብዙውን ጊዜ አደጋን ለመሸሽ ማህበራዊ ትስስር ይፈጥራሉ እናም ለሥነ ምግባር ጥሰቶች ተጨማሪ ማህበራዊ ቅጣት ሊጣልባቸው ይችላል።
- በስልጣን ላይ ያሉ ሴቶች የሴቶችን ጥቅም በጉልህ ለመወከል፣ በ"የሴቶች ጥቅም" የፖሊሲ ዘርፎች ውስጥ የህዝብ ንብረቶችን እና አገልግሎቶችን አቅርቦት ያሻሽላሉ፤ ይህም በእነዚያ ዘርፎች ውስጥ ሙስናን ለመቀነስ ይጠቅማል።

**ለፖሊሲ አወጣጥ ይህ የሚያመለክተው:**

- የፆታ ኢ-እኩልነት በሚኖርበት ጊዜ ሙስናን መቀነስ ችግሩን ለመቀነስ ይረዳል
- የፆታ አለመመጣጠን በሚኖርበት ጊዜ የሴቶች ተጨባጭ አቅም ማሳደግ ሙስናን ሊቀንስ ይችላል

ምንጭ: UNODC, The Time is Now: Addressing the Gender Dimensions of Corruption (Vienna, 2020).

## ሙስና እና የአየር ንብረት ለውጥ

በዘላቂ ልማት ግቦች እንደተገለጸው ኢኮኖሚ፣ አካባቢ እና ማህበረሰብ በቅርበት የተሳሰሩ ናቸው። ጤናማ አካባቢ ከሌለ ጤናማ ማህበረሰብ ሊኖር አይችልም፤ እንዲሁም ጤናማ ማህበረሰብ ከሌለ ጤናማ ኢኮኖሚ ሊገነባ አይችልም። በመሆኑም የአካባቢ ጥበቃ ዘላቂ እና የተሻለ ማህበረሰብና ኢኮኖሚ መሠረት ነው። እ.ኤ.አ. በጥቅምት 2021 የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት ንጹሕ እና ጤናማ አካባቢ የማግኘት መብትን በተመለከተ ውሳኔ 48/13 አጽድቋል። በዚህ ውሳኔ ውስጥ ዘላቂ ልማት በሦስቱ አቅጣጫዎች - ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ - ለሰው ልጅ ደህንነት እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝቧል።

የተባበሩት መንግስታት እንደገለጸው የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም አቀፍ ሥነ-ምህዳር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ ሲሆን የዓለማችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ እየቀረጸ ይገኛል። ከባድ የአየር ሁኔታ ክስተቶች[18] ለሰው ልጅ የአየር ንብረት ቀውስ አስቸኳይነት የሚያሳስቡ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። ብዙ አገሮች የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀት መጨመር፣ የባህር ከፍታ መጨመር እና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰት መፈናቀልን ጨምሮ የሚያጋጥሙ ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም የመላመድ እርምጃዎችን እና የኪሳራና ጉዳት መቀነሻ ስልቶችን እየተጠቀሙ ነው። በዚህ አውድ ውስጥ ሙስና እየጨመረ የመጣ ስጋት ሲሆን የአየር ንብረት አጀንዳዎችን ውጤታማ ትግበራ ሊያደናቅፍ፣ ሊያዳክም እና ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል።

ሙስና ለደን መጥፋት እና ለአየር ንብረት ቀውስ አስተዋፅዖ ሊያደርግ ይችላል[19] ። በተጨማሪም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ጥረቶችን ሊያደናቅፍ ይችላል። ለምሳሌ የቁጥጥር እጥረት እንደ ካርቦን ክሬዲት ገበያዎች ያሉ የካርቦን ማካካሻ ዕቅዶችን ለሙስና ተጋላጭ ያደርጋል። ሙስና የአየር ንብረት ፋይናንስን ተደራሽነትና አቅርቦት ሊያደናቅፍ፣ የፖለቲካና የሕግ መዋቅሮችን ሊያዳክም፣ የብዝሃ ሕይወት መጥፋትን ሊያባብስ እና የአካባቢ ጥበቃ ተከላካዮችን እና ተጎጂ የሆኑ ማህበረሰቦችን ሕይወትና ኑሮ ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል። በመሆኑም በአየር ንብረት ለውጥ አውድ ውስጥ ሙስናን መዋጋት የአየር ንብረት እርምጃዎች ግልጽነትና ውጤታማነት እንዲጠበቅ እንዲሁም አካባቢንና የአገሬው ተወላጆችን ከህገ-ወጥ ተግባራት ለመጠበቅ ወሳኝ ነው። ከአየር ንብረት ለውጥና ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዘ ሙስና በፋይናንስ ግልጽነት እጥረት ሊከሰት ይችላል፤ እንዲሁም ለአየር ንብረት ፕሮጀክቶች የተመደበ ገንዘብ በአላግባብ ጥቅም ላይ መዋል ወይም የመዝረፍ መልክ ሊይዝ ይችላል።[20]

### በማሌዥያ ውስጥ የአየር ንብረት ፈንድ ሙስና እና አላግባብ መጠቀም

እ.ኤ.አ. በ 2022 የቀድሞው የማሌዢያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ ጥረቶች የተመደበውን ገንዘብ ጨምሮ ከብሔራዊ ልማት ፈንድ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን አላግባብ በመጠቀማቸው ተከሷል።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር እና የህዝብ እምነትን መጣስን ጨምሮ በሁሉም ክሶች ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተዋል። እነዚህ ሁሉ ከቀድሞው የልማት ፈንድ ክፍል በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ሂሳብ ውስጥ ከተቀመጠው የ10 ሚሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ ጋር የተያያዙ ናቸው።

ምንጭ : Reuters, “Explainer: Malaysia’s ex-PM Najib and the multi-billion dollar 1MDB scandal”, 23 August 2022.

ወደ ፊት ስንሄድ በአየር ንብረት ለውጥ እና በፀረ-ሙስና መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ማተኮር እና የሚያስከትሉትን ችግሮች ለመፍታት ተገቢ እና ዘላቂ ስልቶችን መንደፍ አለብን። ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ሙስናን መቀነስ አለመቻል የእነዚህን ድርጊቶች ውጤታማነት ከማዳከም ባለፈ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል። እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ላይ የሚያሳድረውን እኩልነት ሊያባብሰው ይችላል።

ስለ ሙስና እና የአየር ንብረት ለውጥ የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ በአትላንታ፣ ጆርጂያ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የተካሄደውን በተባበሩት መንግስታት የፀረሙስና ኮንቬንሽን አባል ሀገራት ኮንፈረንስ (Conference of the States Parties) አሥረኛው ክፍለ ጊዜ ላይ የቀረበውን የዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ እና የዓለም ባንክ ቡድን ወረቀት እንዲያነቡ እንመክራለን፡ “Discussion draft for the Conference of the States Parties to the Convention: Addressing the links between corruption and the response to climate change”

18 Jeff Masters, “World rocked by 29-billion-dollar weather disasters in 2022”, Yale Climate Connections, 19 October 2022.

19 UNODC, Rooting Out Corruption: An Introduction to Addressing the Corruption Fuelling Forest Loss (Vienna, 2023).

20 UNODC and World Bank Group, “Addressing Corruption Risks to Safeguard the Response to Climate Change: Discussion Draft II” (2023).

## ሙስና እና አካል ጉዳተኝነትን ማካተት

አካል ጉዳተኞች ሙስናን ለመቃወም እና በተለያዩ መንገዶች እርምጃ ለመውሰድ ከሌሎች ቡድኖች ይልቅ ዝቅተኛ አቅም እንዳላቸው ሊሰማቸው ይችላል። ይህም በመሆኑ ብዙውን ጊዜ የተወሰኑ የምርጫ አማራጮች፣ የመረጃ ተደራሽነት እጥረት፣ ውስን ሀብቶች እና ስጋታቸውን ለመግለጽ ብዙ እድሎች ስለሌሏቸው እንዲሁም በብዙ ሁኔታዎች በሌሎች ላይ ጥገኛ ስለሚሆኑ ነው።

> **የ"አካል ጉዳተኛ" ትርጓሜዎች**
>
> በየአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን (UNCRPD) አንቀጽ 1 መሠረት፣ "አካል ጉዳተኞች" ማለት ከተለያዩ መሰናክሎች ጋር በመስተጋብር ምክንያት በህብረተሰብ ውስጥ ሙሉ፣ ውጤታማ እና እኩል ተሳትፎ ማድረጋቸው ሊደናቀፍ የሚችል፣ የረጅም ጊዜ የአካል፣ የአእምሮ፣ ወይም የስሜት ሕዋሳት እክል ያለባቸው ሰዎች ማለት ነው።
>
> ስለዚህ፣ "አካል ጉዳተኞች" የሚለው ቃል "ሰውን በቅድሚያ የሚያስቀምጥ" (people-first language) አቀራረብን ያንጸባርቃል። ይህም ሰውነትን በቅድሚያ በመግለጽ የአካል ጉዳትን በኋላ የሚጠቅስ አገላለጽ ነው። ሆኖም ይህ ብቸኛው ተቀባይነት ያለው አገላለጽ አይደለም። ለምሳሌ፣ አንዳንድ የአካል ጉዳተኞች ኔትወርኮች፣ እንደ European Network on Independent Living (ENIL)፣ "Disabled Person" የሚለውን ቃል ይመርጣሉ። ይህም የአካል ጉዳት የሚፈጠረው በሰውዬው ሳይሆን በማህበረሰብና በአካባቢ ያሉ መሰናክሎች ምክንያት መሆኑን ለማጉላት ነው።

አካል ጉዳተኞች ተጋላጭ ከሚሆኑባቸው የሙስና ዓይነቶች አንጻር ጥናቶች እንደሚያሳዩት አካል ጉዳተኞች በሚንከባከቧቸው ሰዎች ለብዝበዛና ለተለያዩ ዓይነት ጥቃቶች ሊጋለጡ ይችላሉ። ለምሳሌ ለአካል ጉዳተኞች የተመደበ ገንዘብ መዝረፍ ወይም ማጭበርበር እንዲሁም የአካል ጉዳተኝነት የምስክር ወረቀት በማግኘት ሂደት ውስጥ መበዝበዝ ይገኙበታል።[21] በተጨማሪም በቋሚ ቁጥጥር በሚደረግባቸው ዝግ ተቋማት ውስጥ የሚኖሩ አካል ጉዳተኞች ይህን ዓይነት በደል ሪፖርት የማድረግ አቅም ስለማይኖራቸው የሚገባቸውን አገልግሎቶች ለማግኘት ለነርሶች ወይም ለሌሎች ሠራተኞች ጉቦ እንዲሰጡ ሊገደዱ ይችላሉ።

በተጨማሪም የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮሚቴ (Committee on the Rights of Persons with Disabilities) የየአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አፈጻጸምን በሚከታተልበት ሥራው የአእምሮ እክል፣ የሥነ-ልቦናና ማህበራዊ እክል ያለባቸው ሰዎች እንዲሁም አካል ጉዳተኞዝ፣ ሕፃናት፣ አዛውንቶች እና ሴቶች በተለየ ለስልታዊና መዋቅራዊ መድልዎ ተጋላጭ መሆናቸውን ጠቅሷል። ይህ መድልዎ ለሙስና የበለጠ ተጋላጭነትን ሊያስከትል ይችላል። በእርግጥም ለአድልዎ በበለጠ የተጋለጡ ቡድኖች ከሌሎች ይልቅ የሙስና ሰለባ የመሆን እድላቸው ከፍተኛ ነው ምክንያቱም ሙሰኞች በቀጥታ ኢላማ ሊያደርጓቸው ይችላሉና።

ሙስና እና መድልዎ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ ሲሆኑ መዋቅራዊ እኩልነት ማጣትን ያባብሳሉ እና ያራዝማሉ። በዚህም ምክንያት አካል ጉዳተኞች የሙስና ሰለባ እንዲሆኑ እና ለደህንነታቸው አስፈላጊ ከሆኑ አገልግሎቶችና ሀብቶች እንዲነፈጉ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ።

እነዚህ ምሳሌዎች አካል ጉዳተኞች በሙስና ምክንያት ከባድ ጉዳት ሊደርስባቸው እንደሚችል ያሳያሉ፤ በዚህም ምክንያት ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የበለጠ ድጋፍ፣ አቅም ግንባታ እና ተሳትፎ እንደሚያስፈልጋቸው በግልጽ ያመለክታሉ።

ይሁን እንጂ አካል ጉዳተኞችም እንደማንኛውም ሰው የሙስና ድርጊቶችን ሊፈጽሙ እንደሚችሉ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ይህን መገንዘብ በአካል ጉዳተኝነት ላይ የተመሰረቱ የተሳሳቱ አመለካከቶችንና መድልዎን ለማስወገድ ወሳኝ ነው። በየአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን መሠረት በአካል ጉዳተኝነት ላይ የተመሰረተ መድልዎ ማለት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በባህላዊ፣ በሲቪል ወይም በሌላ ማንኛውም ዘርፍ ሰብአዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን ከሌሎች ጋር እኩል በሆነ መንገድ እውቅና እንዳያገኙ፣ እንዳይጠቀሙባቸው ወይም እንዳይተገብሯቸው የሚያደርግ ማንኛውም ልዩነት ማግለል ወይም ገደብ ነው።

በሥርዓተ-ፆታ ክፍል እንደተብራራው አካል ጉዳተኞችና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ "ከፍተኛ የሥነ-ምግባር ደረጃ ያላቸው" ተደርገው ይታያሉ። ይህ ግን አካል ጉዳተኞች፣ ቤተሰቦቻቸው ወይም ከእነሱ ጋር የሚሠሩ ባለሙያዎች በስግብግብነት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ለሙስና ሊጋለጡ ወይም ሊሳተፉ እንደሚችሉ የሚያሳየው እውነታ ሊሸፍን አይገባም። በቀላል አነጋገር ልክ እንደሌሎች ሰዎች ሁሉ አካል ጉዳተኞችም አዎንታዊና አሉታዊ ባህሪያትና ፍላጎቶች አሏቸው።

በመጨረሻም የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቮችን ሲያዘጋጁና ሲተገብሩ የአካል ጉዳተኝነትን በሁሉም ሂደቶች ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ነው። ከሚተባበሯቸው ድርጅቶች ጋርም የአካል ጉዳተኞችን ማካተት ለማሻሻል እውነተኛና ዘላቂ ቁርጠኝነት እንዳላቸው ማረጋገጥ ይገባል። ለምሳሌ በአካል ጉዳተኞች ስም የሚመደቡ ገንዘቦችንና ሀብቶችን ለግል ጥቅም መዋል ወይም የፕሮግራሞችን ዓላማ በመጠቀም የግል ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት እንዳይውል ተገቢ የቁጥጥር ሥርዓቶች ሊኖሩ ይገባል።

21 Matthew Jenkins and Ellie McDonald, "Corruption and the equal enjoyment of rights for persons with disabilities", U4 Helpdesk Answer 2022, 29 April 2022.


## ሙስና እና አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዓለማችንን በፍጥነት እየቀየረ ነው። ይህም እንዴት እንደምንሠራ፣ እንዴት እንደምንማር እና እርስ በርስ እንዴት እንደምንገናኝ እየቀየረ ነው። አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አወንታዊ አስተዋፅዖ ሊያደርግ ከሚችልባቸው ዘርፎች አንዱ ሙስናን መዋጋት ነው። ባለፉት ዓመታት ቴክኖሎጂ ግልጽነትን ለማሳደግ እንዴት አስተዋፅዖ እንዳደረገ፣ ተጠያቂነትን እንዴት እንዳጠናከረ እና በማህበረሰባችን ውስጥ ንቁ የሲቪክ ተሳትፎን እንዴት እንዳበረታታ አይተናል። በሥነ ምግባር እና በሰብአዊ መብት መርሆዎችና ደረጃዎች መሠረት የተገነባ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ቁልፍ መሣሪያ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።



ሙስናን ለመዋጋት አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን እንዴት መጠቀም እንችላለን?

ይህንን ለማድረግ የምንችልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡-



- **ዳታ አናሊሲስ** - የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ስልተ ቀመሮች እንደ ማጭበርበር ወይም ሌሎች የሙስና ድርጊቶች ያሉ ጥሰቶችን ለመለየት እንደ ግብይቶች ወይም የግዥ መረጃዎች ያሉ ከፍተኛ መጠን ያላቸውን መረጃዎች ለማስኬድ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ከዚህም በላይ ያልተለመዱ ክስተቶች መለየት (anomaly detection) እና የኔትወርክ ትንተና ያሉ የላቁ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኒኮችን በመጠቀም በባህላዊ ዘዴዎች በቀላሉ ሊታዩ የማይችሉ ውስብስብ የሙስና አወቃቀሮችን መለየት ይቻላል።
- **ትንበያ (Predictive) ሞዴሊንግ** - አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በታሪካዊ መረጃዎች ላይ በመመስረት ሙስና ሊከሰት የሚችልባቸውን አካባቢዎች ለመለየት እና ተፅዕኖውን ለመገምገም የሚያስችሉ የትንበያ ሞዴሎችን ለማዘጋጀት ይረዳል። ይህም ፖሊሲ አውጪዎችን እና ማህበረሰቡን የመከላከል ስልቶችን እንዲያዳብሩ ያግዛል፤ ይህም የሙስና ስጋቶችን ለመቀነስ አስቀድሞ እርምጃ እንዲወሰድ ያስችላል።
- **የመረጃ ሰጪዎች ድጋፍ (Whistle-blower Support)** - የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ቻትቦቶች ሊዘጋጁና ሊሰለጥኑ ይችላሉ፤ እነዚህም ሙስናን ለማጋለጥ የሚያስፈልጉ ደህንነቱ የተጠበቁ ሂደቶችን እና የሪፖርት ማቅረቢያ መንገዶችን መረጃ ለመስጠት ሊያገለግሉ ይችላሉ። በተጨማሪም የተፈጥሮ ቋንቋ ማቀነባበር (Natural Language Processing) ችሎታዎችን በመጠቀም በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የተደገፉ ስርዓቶች በመረጃ ሰጪዎች ሪፖርቶች ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ የሙስና ምልክቶችን ለመለየት ከፍተኛ መጠን ያለው የጽሑፍ መረጃ መተንተን ይችላሉ፤ በዚህም የበለጠ ውጤታማ ምላሾችን ለመስጠት ያስችላሉ።
- **ትምህርት እና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ** - አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ስለ የህዝብ አገልግሎቶች፣ ሂደቶች እና ስርዓቶች ጠቃሚ መረጃዎችን ለህዝብ ለማቅረብ ሊያገለግል ይችላል፤ ይህም ስለ ሙስና ግንዛቤን እንዲጨምር እና ለሙስና ተጋላጭነትን እንዲቀንስ ያግዛል። በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሚደገፉ የትምህርት መድረኮች ለተለያዩ የህዝብ ቡድኖች የተስተካከሉ የመማሪያ ልምዶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይህም ግለሰቦች የሙስናን ውስብስብነት እንዲገነዘቡ እና ችግሩን ለመዋጋት በመረጃ የተደገፈ እርምጃ እንዲወስዱ ያስችላቸዋል።

በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዘርፍ ያሉ እድገቶች ሙስናን ለመዋጋት ያለንን አካሄድ ያለማቋረጥ እየቀረጹ ነው። ለምሳሌ በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሚስጥራዊ መረጃዎችን ደህንነት እና ግላዊነት ለማሳደግ እንደ ብሎክ ቼን እና ፌዴሬትድ ለርኒንግ ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ስርዓቶች ጋር እየተቀላቀሉ ነው። የብሎክ ቼን ቴክኖሎጂ ለትንተና እና ለውሳኔ አሰጣጥ

ጥቅም ላይ የሚውለውን መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ tamper-proof verification እና ግልጽ የመዝገብ አያያዝን ሊያቀርብ ይችላል። ፌዴሬትድ ለርኒንግ ደግሞ በበርካታ ያልተማከለ የመረጃ ምንጮች ላይ የትብብር ሞዴል ስልጠናን ያስችላል፤ ይህም የግለሰብ መረጃዎችን ምስጢራዊነት በመጠበቅ የሙስና ቅጦችን ለመለየት የጋራ ግንዛቤዎችን ለማግኘት ያግዛል። እነዚህን ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በመቀበል፣ በፀረ-ሙስና ጥረታችን ውስጥ የበለጠ ውጤታማነትንና ቅልጥፍናን ማሳደግ እንችላለን፤ ከተለዋዋጭ ተግዳሮቶች ቀድመን በመቆየት እና የማህበረሰባችንን ታማኝነት በመጠበቅ። እነዚህ ጣልቃ ገብነቶች በአግባቡ ከተተገበሩ በህብረተሰባችን ውስጥ ያለውን የሙስና መጠን ለመቀነስ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ይሁን እንጂ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ሙስናን በምንካሄደው ትግል ብቸኛ መፍትሄ እንዳልሆነ ማስታወስ ጠቃሚ ነው፤ ከሌሎች ትርጉም ያላቸው ዘዴዎች እና ተግባራት ጋር በማዋሃድ መጠቀም ይገባል።

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን መጠቀም በጥረታችን ውስጥ ጠቃሚ መሆኑን ብንገነዘብም እነዚህ ቴክኖሎጂዎች እና ስልተ ቀመሮች ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጡ መንገዶች የተገነቡ እና ከሥነ ምግባር እሴቶች እና ከሰብአዊ መብቶች መርሆዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ልንጠይቅ ይገባል።

አሁን ያነበቡት ክፍል በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የተፈጠረ መሆኑን ያውቃሉ? በዚህ ቱልኪት ውስጥ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን መጠቀም እንደ ሙስና ያሉ ውስብስብ ጉዳዮችን ለመፍታት ያለውን አቅም ከማሳየት ባለፈ ቴክኖሎጂን ለአዎንታዊ ለውጥ የመጠቀም አስፈላጊነትንም ያሳያል። ይህን ቱልኪት ሲያነቡ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የወደፊት ሮቦቶች ብቻ እንዳልሆነ ያስታውሱ፤ ነገር ግን ለሁሉም ሰው የበለጠ ብሩህ እና ግልጽ የሆነ የወደፊት ጊዜ ለመገንባት የማሰብ ችሎታ ያላቸውን ስርዓቶች በኃላፊነት መጠቀም ነው።

እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች በቱልኪቱ ውስጥ ቢካተቱም ይህ ሙሉ ዝርዝር እንዳልሆነ ማወቅ አለባችሁ። ለምሳሌ በስፖርት ዘርፍ ያለው ሙስና፣ በጤና ዘርፍ ያለው ሙስና፣ በግሉ ዘርፍ ውስጥ ያለው ሙስና እና ሌሎች ጉዳዮችን በመመርመር ተጨማሪ ትስስሮችን ማግኘት ይቻላል። ስለዚህ የሚወዱት ርዕስ በዚህ ቱልኪት ውስጥ ከሌለ አትጨነቁ፤ በመስመር ላይ ምርምር በማድረግ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች እርምጃዎችን ወደ ኢኒሼቲቫችሁ ማካተት ትችላላችሁ።

**ስለ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ እና ሙስናን በመዋጋት ረገድ ስላለው ሚና የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?**

ለእናንተ የመረጥናቸው አንዳንድ ምንጮች እነኚሁና

- Nils Köbis and others, “Artificial intelligence as an anti-corruption tool (AI-ACT) – potentials and pitfalls for top-down and bottom-up approaches”, academic paper, Germany, February 2021.
- Nils Köbis and others, “The promise and perils of using artificial intelligence to fight corruption” by Nils Köbis, Christopher”, Nature Machine Intelligence, vol. 4, No.5 (May 2022), pp.418-424.
- Transparency International, “The Corruption Risks of Artificial Intelligence” (2022).
- Vinay Sharma, “Can artificial intelligence stop corruption in its tracks?”, World Bank Blogs, 15 November 2018.
- Coalition for Integrity, Using Machine Learning for Anti-Corruption Risk and Compliance (2021).

# 03: አውዳዊ አገባብ አድርጉ

አሁን ስለ ሙስና ምንነትና የሚያስከቲላቸውን ችግሮች አውቃችሁ ትኩረት የምታደርጉበትን ርዕስ መርጣችኋል፤ እንዲሁም ሙስና ከሌሎች ዘርፎች ጋር የሚገናኝባቸውን አንዳንድ መንገዶች ተረድታችኋል። በመቀጠልም ጉዳዩን በተገቢው አውድ ውስጥ ለማስቀመጥ ዝግጁ መሆን ይገባችሁዋል።

ሙስናን ለመዋጋት ጉዟችሁን መጀመር ከባድ ስራ ሊመስላችሁ ይችላል፤ በተለይም ባላችሁ ችሎታ እና ጊዜ መጠን ላይ በመመስረት። ሆኖም እያንዳንዱ ትንሽ እርምጃ ጉልህ ለውጥ የማምጣት ኃይል እንዳለው ልናስታውሳችሁ እንፈልጋለን። የአካባቢያችሁን ቋንቋዎችና ባህሎች ከፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁ ጋር ማዋሃድ አስፈላጊ ነው። ሀሳባችሁ ይበልጥ ተዛማጅ እና ለሰዎች ልብ የቀረበ በሆነ መጠን ሌሎች ወጣቶችን የማነሳሳት አቅሙም የበለጠ ይሆናል። ስለዚህ ጉዳዩን በአውድ ውስጥ በማስቀመጥ መጀመር ይገባችኋል።

የመረጣችሁት የሙስና ጉዳይ በምትኖሩበት ቦታ ወይም በምትፈልጉት አውድ ውስጥ እንዴት እንደሚገኝ ለመረዳት ይህ ጉዳይ በማህበረሰባችሁ፣ በከተማችሁ፣ በሀገራችሁ ወይም በክልላችሁ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመመርመር ልትፈልጉ ትችላላችሁ። በዚህ የጉዟችሁ ክፍል በመረጣችሁት አውድ ውስጥ ስለ ሙስና እና ከመረጣችሁት ርዕስ ጋር በተያያዘ ጥናት ማካሄድ ትፈልጉ ይሆናል። በጠረጴዛ ላይ የተመሰረተ ምርምር (desk research) ለማካሄድ ከወሰናችሁ የክልል፣ የሀገር ውስጥ እና የቀጠና ሚዲያዎችን መመልከት ትችላላችሁ። እንዲሁም የክልል፣ የሀገር ውስጥ እና የቀጠናዊ የመረጃ ጎታዎችን በመጠቀም ምርምር ማካሄድ ትችላላችሁ፤ ይህ ማለትም የመንግስት ድረ-ገጾችን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ የአካዳሚክ ምንጮችን እና የዓለም አቀፍ ድርጅቶችን ሪሶርሶች ማካተት ይችላል።

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እና ሀሳቦቻችሁን ለማዳበር ሌላው መንገድ በማህበረሰባችሁ ውስጥ ያሉ ሰዎችን መጠየቅ ነው። ሙስና ስሜታዊ እና ሚስጥራዊ ጉዳይ ሊሆን ስለሚችል ከምታምኗቸው ሰዎች ጋር በመነጋገር መጀመር ይገባል። በቃለ መጠይቅ ከሰዎች መረጃ ለመሰብሰብ ከወሰናችሁ ጥያቄዎቻችሁ የምትፈልጉትን መረጃ በግልጽ መንገድ እንዲያገኙ በሚያስችል መልኩ መዘጋጀት አለባቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ የምትማሩትን ነገር መከታተላችሁን አረጋግጡ፤ ምክንያቱም ይህ በፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁ እድገት ውስጥ ጠቃሚ ይሆናል። ሁልጊዜ ቅድሚያ ፈቃድ መጠየቅን ሳትዘነጉ ከሰዎች ጋር የምታደርጉትን ውይይቶች መመዝገብ፣ ማስታወሻ በመያዝ ወይም ከእያንዳንዱ ቃለመጠይቅ በኋላ አስተያየታችሁን በመጻፍ ይህንን ማድረግ ትችላላችሁ። የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችን እንዴት መቅረጽ እንደሚቻል ተጨማሪ ምክሮች በቱልኪቱ የመጨረሻ ክፍል "የመጨረሻው ጉርሻ: ስራችሁን ገምግሙ እና ተጽእኖውን ያሳውቁ" በሚለው ክፍል ውስጥ ይገኛሉ።

### የፖለቲካል ኢኮኖሚ ትንተና ምንድን ነው? እንዴትስ ልንጠቀመው እንችላለን?

የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንተና[22] የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንተና  በህብረተሰብ ውስጥ ባሉ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ሂደቶች መካከል ያለውን መስተጋብር እና ግንኙነት ይመለከታል። ይህም በተለያዩ ቡድኖች እና ግለሰቦች መካከል ያለውን የሀይል እና የሀብት ክፍፍል እንዲሁም እነዚህን ግንኙነቶች በጊዜ ሂደት የሚፈጥሩ፣ የሚደግፉ እና የሚቀይሩ ሂደቶችን ያጠናል።

የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንተናን መጠቀም በአንድ የተወሰነ አውድ ወይም ችግር ላይ "የጠለቀ እይታን" በመጠቀም ለመመርመር የሚያስችል መንገድ ነው። አስቸጋሪ ቢመስልም የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንተና ልዩ ክህሎቶች ላይ የሚያተኩር አይደለም፤ ይልቁንም ትክክለኛ ጥያቄዎችን መጠየቅ ላይ ያተኩራል።



የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንተናን ለማካሄድ አንድ የተወሰነ ንድፍ እንደሌለ እና ድርጅቶች እና ግለሰቦች የተለያዩ አቀራረቦችን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ማስታወስ ያስፈልጋል። ሆኖም ይህ አቀራረብ በአጠቃላይ ሁለገብ ሲሆን ሁለቱንም የጥራት እና የመጠን መረጃዎችን ይጠቀማል።

በብዛት የሚጠቀሱ ዋና ዋና ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፦

- **የባለድርሻ አካላት ትንተና።** ይህ የተለያዩ ቡድኖችን ዳሰሳ በማዘጋጀት (mapping) በፖሊሲዎች ወይም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ለመረዳት የሚጠቅም ነው። ይህ ትንተና የተወሰኑ ቡድኖች ወይም ተዋናዮች የለውጥ ሂደቶችን ለመደገፍ ወይም ለመቃወም ያላቸውን እድል ለመረዳት ያስችላል።
- **ሰፊውን የፖለቲካ አውድ ትንተና።** ይህ መሳሪያ የፖለቲካ ስርዓቱን ዋና ዋና አካላት ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ያላቸውን ጉዳዮች ለመረዳት ያስችለናል።
- **መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ (formal and informal) ተቋማት ትንተና።** ይህ በለውጥ ሂደቶች ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ለመረዳት በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ ተቋማት መካከል ያለውን ስልጣን እና ተፅዕኖ ለመመደብ ያስችላል።
- **አደጋዎችን መለየት እና መቀነስ።** ይህ መሳሪያ አንድ ፖሊሲ ወይም ፕሮጀክት በተለያዩ ቡድኖች ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ለመረዳት ይረዳል። የለውጥ ሂደቶች የተለያዩ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ቡድኖችን በተለያየ መንገድ ሊነኩ እና ውጥረትን፣ ግጭትን ወይም ለውጥን መቋቋምን ሊያስከትሉ ይችላሉ።
- ለፖለቲካ ኢኮኖሚ ትንተና ተጨማሪ ምሳሌዎችን ለማግኘት የ U4 Anti-Corruption Resource Centre ድህረ ገጽ እና ሪሶርሶች ተመልከቱ።

22 U4 Anti-Corruption Resource Centre, "U4 Expert Answer – Political economy analysis of anti-corruption reforms" (2009).

### ለቃለ መጠይቅ ሌላ ጠቃሚ መሳሪያ በቀጣይ ቀርብዋል:

**ክዋንቲቴቲቭ ኢንተርቪው**

ሰዓት: 10 ደቂቃ

ስለ..... ንገረኝ (ቴል ሚ አባውት...)

አዎንታዊ፣ አሉታዊ፣ እና አስገራሚ ተሞክሮዎች

ለምን?

ምኞቶች እና ፍላጎቶች

በቃለ መጠይቁ ወቅት የተስተዋሉ ምልክታዎች

# 04: ንድፍ አውጡ

አንዴ በመረጣችሁት አውድ ውስጥ ከዘርፋችሁ ጋር የተያያዘውን የሙስና ሁኔታ በተሻለ ሁኔታ ከተረዳችሁ በኋላ ቀጣይ እርምጃችሁን ለማቀድ መጀመር ትችላላችሁ።

1. **ችግሩን በመግለጽ ጀምሩ:** የለያችሁትን ዘርፍ ውስጥ ሙስናን በግልጽ ለመግለጽ እና ለመፍታት እንዲሁም የምትፈልጉትን ችግር ለመረዳት ከላይ የተማራችሁትን ተጠቀሙ።

**ምሳሌ:**

በማህበረሰቤ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ሙስናን በመዋጋት ረገድ ያላቸውን ሚና በደንብ አይረዱም። ብዙውን ጊዜምንም ማረግ እንደማይችሉ ይሰማቸዋል፤ እናም ለአጠቃላይ ለውጥ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይታይባቸዋል። አንዳንድ ሰዎች ሊደርስባቸው የሚችለውን የበቀል እርምጃን በመፍራት ወይም ሪፖርት አለማድረግ ጥቅማጥቅሞችን ያስገኛል ብለው በማሰብ ሙሰኛ ግለሰቦችን ይከላከላሉ። በዚህም ምክንያት ሊከላከሉ የሚችሉ። በርካታ ሙስናዎች አሁንም እየቀጠሉ ይገኛሉ። ይህ በተለይ ወጣቶች ጊዜያቸውን በሚያሳልፉባቸው ቦታዎች እንደ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ጎልቶ ይታያል።

2. **መፍትሄው ምንድን ነው?** ብቻችሁን ወይም በቡድን ሆናችሁ የመረጣችሁት ሀሳብ የለያችሁትን ችግር እንዴት መፍታት እንደሚችል ለመግለጽ ጊዜ ውሰዱ።

**ምሳሌ:**

የእኔ ሀሳብ በማህበረሰቤ ውስጥ ባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለመስራት ነው። ትምህርት ቤታችሁ ወይም ዩኒቨርሲቲያችሁ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚቀበል እና ምን እንደሚያወጣ አስባችሁ ታውቃላችሁ? የህዝብ ነው ወይስ የግል የገንዘብ ድጋፍ? እንደ መጻሕፍት እና ኮምፒውተሮች ያሉ ለተማሪዎች የሚቀርቡ ሌሎች ሪሶርሶች አሉ? እንዴትስ ነው የሚገዙት እና የሚተዳደሩት? በዚህ ሂደት ውስጥ ብክነት ይታይበታል? ገንዘቡ የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልበት መንገድ አለ? ተማሪዎቹ ገንዘቡን እንዴት እንደሚውል በመከታተል እና በመወሰን ላይ መሳተታቸው አስፈላጊ ነው?

**ምሳሌ:**

ዋና ትኩረት የምሰጥበት በማህበረሰቤ ውስጥ ያሉ ሦስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ናቸው። የተማሪዎቹ ዕድሜ ከ 15 እስከ 18 ዓመት መሆን አለበት።

**ዲዛይን ቲንኪንግ ምንድን ነው?**

ዲዛይን ቲንኪንግ ሰውን ማዕከል ያደረገ አንድ ብቻ መስመርን የማይከተል እና አይተሬቲቭ የንድፍ ሂደት ነው። ግምቶችን በመፈተሽ፣ የፈጠራ መፍትሄዎችን በመተግበር፣ ፕሮቶታይፖችን በማዘጋጀት እና በመሞከር ያልተገለጹ ወይም ያልታወቁ ችግሮችን በጋራ የሚፈታበት አቀራረብ ነው።

3. **ለሃሳባችሁ የአዕምሮ እቅድ (mind map) ፍጠሩ:** የቪዡዋላይዜሽን መሳሪያዎችን መጠቀም ሀሳባችሁ በተግባር እንዴት ሊሰራ እንደሚችል ለማየት ይረዳችኋል። ይህንን ለማድረግ ስለ ተግባራዊነቱ፣ ስለሚያስፈልጉ ሪሶርሶች እና ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ተግዳሮቶች ለማሰብ የሚረዱ ተከታታይ ጥያቄዎችን መመለስ ትችላላችሁ። እነዚህ ኢኒሼቲቫችሁን በዝርዝር ለመንደፍ የሚረዷችሁ ጥቂት ጥያቄዎች ናቸው። ሆኖም እናንተን የበለጠ ለመደገፍ በድህረ-ገጻችን ላይ ብዙ ሪሶርሶችን ይገኛሉ። አንዱ የዲዛይን ቲንኪንግ ዘዴ ላይ የተመሰረተውን ከዚህ በታች ያለውን የፅንሰ ሀሳብ ፖስተር መጠቀም ነው።

- ይህንን ሃሳብ በተግባር ላይ ማዋል የምንችለው እንዴት ነው?
- ምን አይነት ሀብቶች (ጊዜ፣ የሰው ኃይል፣ ወዘተ) አላችሁ?
- ምን መርጃዎች ቀድሞውኑ ይገኛሉ?
- ማንን ማሳተፍ አለብን?
- ማን ሊረዳን ይችላል?
- ከዚህ ጉዳይ በላይ ምን ማወቅ አለብን?
- ምን ተጨማሪ ምርምር መደረግ አለበት?
- ምን ያህል ጊዜ እንፈልጋለን?

**ምሳሌ:**

በመረጥክዋቸው ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን በመረጃ ነፃነት እና በማህበረሰብ ክትትል ላይ በማሰልጠን የትምህርት ቤት ሪሶርሶችን እንዲጠቀምሙ ማገዝ። የማህበረሰብ ዳሰሳ ውጤቶችን በመጠቀም የትምህርት ቤት መምህራንን እና አስተዳደሩን ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዲያዳብሩ እና ተማሪዎችን በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ማሳተፍ እንዳለባቸው ማስገንዘብ።

- በትምህርት ቤት ከ20 እስከ 25 ተማሪዎችን ለዩ
- የሥልጠና ዘዴን አዘጋጁ
- ስልጠናውን አካሂዱ
- በመደበኛ ክትትይ (ምናልባትም በዋትስአፕ ግሩፕ) የሥልጠናውን ውጤቶችና ያመጣውን ለውጦች ተከታተሉ
- በክትትል ውጤቶቹ ላይ በመመርኮዝ ግንዛቤ የማስጨበጫ እንዲሁም ኮሚውኒኬሽን ተኮር ሶስት ወይም ከዚያ በላይ አውደ ጥናቶችን (ወርክሾፖችን) ያዘጋጁ

ይህ እንቅስቃሴ የአሰልጣኞችን እና የፕሮጀክት አስተባባሪዎችን እውቀት፣ ልምድ እና ድጋፍ ይፈልጋል። እንዲሁም ከትምህርት ቤቶች ጋር መገናኘት እና የመምህራን እና የአስተዳደሩን ቁርጠኝነት ማግኘት ያስፈልጋል። በተጨማሪም ተማሪዎቹ በሂደቱ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ተነሳሽነት ማሳደግ አስፈላጊ ነው።

4. **ተግዳሮቶችን እና አደጋዎችን መለየት:** ስራችሁን ከመጀመራችሁ በፊት ምን እክሎች ሊያጋጥምዋችሁ እንደሚችል በጥልቀት ማሰብ አስፈላጊ ነው። ይህም ሊከሰቱ የሚችሉ ተግዳሮቶችን አስቀድሞ በመለየት እና በመቀነስ ስራችሁን በተገቢው ሁኔታ እንድታቅዱ ይረዳችኋል።

**ምሳሌ:**

መምህራኑ እና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ግልጽነትን የሚጠይቀውን ተነሳሽነት ላይወዱት ይችላሉ። ይህም የበቀል እርምጃዎችን ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህ ተማሪዎቹ መብቶቻቸውን በሚገባ ማወቅ አለባቸው፤ ይህም የሥልጠናው ጠንካራ አካል መሆን አለበት። በተጨማሪም በአሰልጣኙ እና በፕሮጀክቱ አስተባባሪ ድጋፍ ተማሪዎቹ ከአካባቢው ፖሊስ፣ ከአካባቢው የሃይማኖት መሪዎች፣ ከመገናኛ ብዙኃን፣ ከመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ከማዘጋጃ ቤት ኃላፊዎች ድጋፍ በመጠየቅ ከትምህርት ቤቱ ጋር ውይይት ማድረግ እና ኢኒሼቲቫቸውን ማስተዋወቅ ይችላሉ።

## ለሰዎች ስለመግጠራ (Innovating for People)

የአክቲቪቲ ቴምፕሌት

ጽንሰ-ሐሳቡ ምን ይባላል?

ለማን ነው?

ምን ችግር ይፈታል?

ትልቁ ሀሳብ ምንድነው?

እንዴት እንደሚሰራ አስረዳ

ለምን ላይሳካ ይችላል?

ምን አይነት ፕሮቶታይፕ እና ሙከራ ማድረግ አለብን?

ስኬትን እንዴት መለካት እንችላለን?

ይህንን እንዴት እናሳካዋለን?

# 05: የፈጠራ ችሎታችሁን አጠናክሩ

ሙስናን ለመዋጋት የሚደረግ እያንዳንዱ ጥረት ዋጋ አለው። እንደሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ሁሉ ሙስናም ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩንና ዘዴዎቹን ይቀይራል። ስለዚህ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎችም ተለዋዋጭ እና ከማህበራዊ ለውጦች ጋር የሚሄዱ መሆን አለባቸው። የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁን የበለጠ ተፅዕኖ ያለው ለማድረግ ያላችሁን የፈጠራ ችሎታ ተጠቀሙ። ለምሳሌ ሥነ-ጥበብ፣ ስፖርት፣ ሙዚቃ፣ ተረት፣ ብሎግ፣ ፖድካስት፣ ቪዲዮ፣ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ሌሎች የፈጠራ መንገዶችን በመጠቀም መልእክታችሁን የበለጠ ተደራሽ ማድረግ ትችላላችሁ።

በአሁኑ ጊዜ ሰዎች በተደጋጋሚነት ለሚታየው ባህላዊ የመረጃ አቀራረብ ብዙም ትኩረት አይሰጡም። ስለዚህ ተሳትፎን የሚያበረታቱ፣ የሚያስተምሩ እና የሚያነሳሱ ፈጠራዊ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። ሰዎች መልእክታችሁን ተረድተው የራሳቸው እንዲያደርጉት ለማገዝ አተሳታፊ እና ማራኪ የግንኙነት መንገዶችን ይጠቀሙ። ይህንን ለማሳካት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና ዲጂታል መድረኮችን በፈጠራ መጠቀም ትችላላችሁ። ለምሳሌ፡-

| የፈጠራ መሳሪያዎች | ዓላማዎች | ምሳሌዎች | የእድሜ ክልል |
|---|---|---|---|
| ቨርቹዋል ሪያሊቲ እና ኦግመንትድ ሪያሊቲ | ገንዘብ ማሰባሰብ<br>ተደራሽነት (outreach)<br>ኮሚውኒኬሽን | ኪዮስኮች<br>ሜታቨርስ<br>የኦግመንትድ ሪያሊቲ ፊልተርስ<br>የቨርቹዋል ሪያሊቲ ኢኖቬሽን<br>የማየት እክል ላለባቸው ሰዎች ማሳተፍ ላይ አውደ ጥናቶች ማድረግ | |
| ሚዲያ | ግንዛቤን ማስጨበጥ<br>መንስኤዎችን ማስተዋወቅ (promoting causes) | ፖድካስቶች<br>ኦንላይን ስትሪሚንግ<br>የOp-ed አርቲክሎች<br>ማህበራዊ ሚዲያ ቭሎጎች<br>የብሬይል ፖስቶች እና ተደራሽ ኮንቴንቶች | በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች |
| ሥነ ጥበብ | ግጭቶችን መተርጎም፣ መግለጽ እና መፍታት<br>አንገብጋቢ ጉዳዮችን (pressing issues) መተርጎም፣ መግለጽ እና መፍታት | ተጨባጭ (tangible) የጥበብ ስራዎች (እንደ ቅርጻ ቅርጾች)<br>ኮሚክ መጽሐፍት<br>ሙዚቃ<br>ፊልሞች<br>የግድግዳ ላይ ስዕሎች<br>ፍላሽሞብ<br>ፎቶቡክስ | |
| ተደጋጋሚ ክስተቶች (trends) | የፀረ-ሙስና መፈክሮችን ማሰራጨት፣ የህዝብ ተሳትፎን ማበረታታት | የፋሽን ዲዛይኖች<br>ቫይራል የኢንተርኔት ኮንቴንቶች<br>የኦዲዮ ኮድ-ግጥም ውድድሮች | ለሁሉም ሰው |
| ስፖርት | ተነሳሽነትን እና ፈጠራን ለመጨመር አካላዊ እና አእምሯዊ ጉልበት ያመነጫሉ | የገቢ ማሰባሰቢያ ውድድሮች<br>ማራቶን<br>የፓራሊምፒክ ጨዋታዎች | |

### ኦፍላይን የሚደረግ ፈጠራ እና ኢኖቬሽን

የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁን በአካል በሚካሄዱ ፕሮግራሞች ለማቅረብ ከወሰናችሁ በፊት መልእክታችሁን በፈጠራ የምታስተላልፉባቸው አማራጮች ብዙ ናቸው። ዛሬ ግራፊቲ፣ ስትሪት አርት፣ 3D የግድግዳ ስዕሎች፣ ሙዚቃ፣ ድራማ እና ሌሎች የሥነ-ጥበብ መንገዶች ወጣቶች ሀሳባቸውን እና ድምፃቸውን የሚያጋሩባቸው ትልልቅ መድረኮች ሆነዋል። እንደ ባንክሲ (Banksy) እና ሼፓርድ ፌሪ (Shepard Fairey) ያሉ የሥነ-ጥበብ አቀንቃኞች ጥበብን ለማህበራዊ ለውጥ መሣሪያ አድርገው በመጠቀም ለብዙዎች መነሳሳት ሆነዋል። እንዲህ ያሉ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን ማካሄድ የማይቻል ቢሆንም በትምህርት ቤታችሁ፣ በድርጅታችሁ ወይም በማህበረሰባችሁ ውስጥ ህጋዊ ፈቃድ በማግኘት የግድግዳ ስዕሎች፣ ፖስተሮች፣ የጥበብ ኤግዚቢሽኖች ወይም የሕዝብ ማሳያዎችን ማዘጋጀት ትችላላችሁ። ማንኛውንም እንቅስቃሴ ስታካሂዱ የአገራችሁን ሕጎች ማክበር እና አስፈላጊውን ፈቃድ ማግኘት እንዳትረሱ።

### ብሬንስቶርሚንግ፡ ሙስናን ለመዋጋት ጥበባዊ አቀራረብ ለምን ውጤታማ ነው?

ሥነ-ጥበብ ሀሳቦችን ለማስተላለፍ፣ ስሜት ለመፍጠር እና ሰዎችን ለመነሳሳት ከፍተኛ አቅም አለው። “አንድ ምስል ከሺህ ቃላት ይበልጣል” የሚለው አባባልም ይህንን ያሳያል። በተለያዩ ባህሎች፣ ሃይማኖቶች፣ የፆታ ማንነቶች፣ ቋንቋዎች እና የትምህርት ደረጃዎች ያሉ ሰዎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ሥነ-ጥበብ ከቃላት ይልቅ ለብዙ ሰዎች የሚደርስ እና ውይይትን የሚያበረታታ ጠንካራ የግንኙነት መሣሪያ ሊሆን ይችላል።

የተለመዱ የጥበብ ስራ ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ

- የጥበብ ኤግዚቢሽኖች፣ ፍላሽሞብ፣ የሙዚቃ ውድድሮች እና የስፖርት ውድድሮች
- አጭር የፊልም ፌስቲቫሎች፣ ኦፕን ማይክ ዝግጅቶች እና የፊልም ምሽቶች

እንዲሁም ከዘላቂ ልማት ግቦች ጋር በሚስማማ መልኩ ኢኒሼቲቫችሁን በፈጠራ እና በጥበብ ስራ እንዴት መተግበር እንደምትችሉ እራሳችሁን ይጠይቁ።




ከናይጄሪያ የመጣችው ዳማሪስ አኪግቤ በጠንካራ የንግግር ግጥሟ - I AM CHANGE - ወጣቶች በአለም ላይ ማየት የሚፈልጉትን ለውጥ እንዴት ሊሆኑ እንደሚችሉ ትናገራለች። [23]



የግድግዳ ሥዕል በShepard Fairey (Obey) – Peace, 2011 & The Birds, Copenhagen, Denmark. Photo: CC BY-NC-SA 2.0 by aestheticssofcrisis.

[23] UNODC, “Rule of Law Champion Damaris Akhigbe”, YouTube, video, 23 April 2020

[24] UNODC, Crime Congress 14, “In Nairobi, youth are talking about corruption, crime prevention and good governance”, 11 December 2018.

## ኦንላይን የሚደረግ ፈጠራ እና ኢኖቬሽን - ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም

ከዓለም ሕዝብ ውስጥ ወደ ሁለት ሦስተኛው የሚጠጋው (62.3 በመቶ) ማህበራዊ ሚዲያን[25] እንደሚጠቀም ከግምት ውስጥ በማስገባት በወጣቶች ዘንድ ስለ ሙስና ግንዛቤ ለማስጨበት ጥሩ መድረክ ሁኖ ይገኛል። ከኮሮና ቫይረስ በሽታ (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ ጀምሮ የማህበራዊ ትስስር መድረኮች ተጠቃሚ ጨምሯል፤ ይህም ለግንኙነት ብዙ እድሎችን ይፈጥራል። ይህ በፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭ ውስጥ ለመጠቀም ጥሩ አጋጣሚ ነው።

### ብሬንስቶርሚንግ፡ ከኦንላይን ፕላትፎርሞች እድገት ጋር እኩል ተራመዱ

ፌስቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ኢንስታግራም፣ ስናፕቻት እና ቲክቶክ በአሁኑ ጊዜ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ናቸው[26]። የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲያችሁን ከማዳበር አንፃር ይህ ምን ማለት ነው?

**ጠቃሚ ምክር:** የተደራሽነት ስትራቴጂያችሁን ስታወጡ እና መልእክቶቻችሁን ስታጋሩ የተለያዩ የማህበረሰብ ቡድኖችን ለመድረስ እነዚህን መድረኮች መጠቀም ትችላላችሁ። ለምሳሌ ዩቲዩብ ፖድካስቶች፣ አፕል ፖድካስቶች፣ ጎግል ፖድካስቶች፣ ሳውንድክላውድ፣ ስፖቲፋይ፣ ዲስኮርድ እና ሌሎች ተመሳሳይ የኦንላይን ይዘቶችን በመጠቀም በሙስና ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር እና ማጋራት ትችላላችሁ።

**ጠቃሚ ምክር:** በማህበራዊ ሚዲያ ላይ “የሥርዓተ-ፆታና የሙስና ልኬቶች” የሚለውን ርዕስ ማንሳት ትፈልጋላችሁ እንበል። ሙስና በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ላይ ስለሚያስከትለው ተፅዕኖ ግንዛቤ ለማሳደግ፣ ተከታታይ ፖስተሮችን፣ ካርቱኖችን፣ የቀልድ መጽሐፎችን፣ ትምህርታዊ ቪዲዮዎችን፣ ቭሎጎችን፣ አጫጭር ሙዚቃዎችን፣ ፊልሞችን እና የአስተያየት (op-ed) መጣጥፎችን በፌስቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ኢንስታግራም፣ ስናፕቻት እና ቲክቶክ አካውንታችሁ ላይ መስራት እና መለጠፍ ትችላላችሁ። እንዲሁም ከዚህ ርዕስ ጋር የተያያዙ ታዋቂ ቁልፍ ቃላትን (ኔትወርኪንግ፣ ፓትሮኔጅ፣ ክላየንታሊስት ቢሄቪየር ወዘተ) በመጠቀም መልእክታችሁን ለወጣት ታዳሚዎች በተሻለ ሁኔታ ማድረስ ትችላላችሁ።

### ሁልጊዜ የምታቀርቡትን መረጃ ከማስተላለፋችሁ በፊት የመረጃውን ትክክለኛነት ያረጋግጡ። የሐሰት መረጃ (Fake News) ከማሰራጨት ይቆጠቡ!

የኦንላይን ደህንነት በእውነተኛ ሕይወት ያለውን ያህል አስፈላጊ ነው። እንዲያውም ሁለቱ ዓለማት በጣም የተሳሰሩ ናቸው፤ ኦንላይን የምታደርጉት ነገር ኦፍላይን ሕይወታችሁ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ስለዚህ የቃላት ምርጫችሁን በጥንቃቄ በማድረግና የኦንላይን አደጋዎችን በሚገባ በማመዛዘን እራሳችሁን ከአደጋ ጠብቁ። ደህንነትን እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ተጨማሪ ሀሳቦችን ለማግኘት በዚህ ሞጁል ክፍል ስምንት እንመለከታለን።




“Keep your coins, I want change”. Stencil by unknown (based on the Banksy stencil). Photo: Beth/flickr.




በኬንያ የተካሄደው የጥበብ ውድድር ወጣት አርቲስቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ ስለ ሙስና መልዕክት አስተላልፈዋል።[24]

[25] Dave Chaffey, “Global social media statistics research summary May 2024”, Smart Insights, 1 May 2024.

[26] Ibid.

## ፈጠራ እና ኢኖቬሽን ሲዋሃዱ

ፈጠራችሁን በመጠቀም የጥበብ ሥራችሁ ዘላቂ እንዲሆን፣ ከሰዎች ጋር እንዲገናኝ እና የበለጠ አሳታፊ ለማድረግ ኦግመንትድ ሪያሊቲ መጠቀም ትችላላችሁ። ኦግመንትድ ሪያሊቲ የመጠቀም መንገዶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ኢመርሲቭ ስቶሪ ቴሊንግ ማህበረሰቡ ሙስናን ጨምሮ ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር በተሻለ ሁኔታ እንዲገናኝ እና በስሜታዊነት እንዲሳተፍ ቪዲዮዎችን በፖስተሮች፣ 2D የግድግዳ ሥዕሎች እና ግራፊቲዎች ላይ ማካተት ትችላላችሁ።
- አሳታፊ ጨዋታዊ (gamified) ዘመቻዎች። ከማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ጋር ለመሳተፍ እና ለማነሳሳት ጌሚፊኬሽንን (Gamification) በአዝናኝ እና ምቹ መንገድ መጠቀም ትችላላችሁ።
- ኦግመንትድ ሪያሊቲ ኪዮስኮች። በገበያ ማዕከሎች፣ በዝግጅቶች እና በትራንስፖርት ማዕከላት (አየር ማረፊያዎች፣ የባቡር፣ የአውቶቡስ እና የሜትሮ ጣቢያዎች) አሳታፊ ጥያቄዎችን እና ጨዋታዎችን በመጠቀም ኢኒሼቲቩን ለማስጀመር እና ለማጠናከር ኦግመንትድ ሪያሊቲ ኪዮስኮችን ማዘጋጀት ትችላላችሁ።
- ማህበራዊ ጋዜጦች እና የማስታወቂያ ሰሌዳዎች። ከታዳሚዎቻችሁ ጋር በተሻለ ሁኔታ ለመግባባት እና ለመገናኘት የማይንቀሳቀሱ የታተሙ የመገናኛ ቁሳቁሶችን ወደ አሳታፊ ይዘት መቀየር ትችላላችሁ።
- ሜታቨርስ። በሜታቨርስ ውስጥ ተስማሚ ምናባዊ ዓለም መፍጠር ትችላላችሁ፤ እንዲሁም በቀጥታ መሳተፍን እና መሳጭ የአቻ ለአቻ የመማር እና የዲጂታል ትምህርት ልምዶችን በመጠቀም እያደገ እና እየጠነከረ የሚሄድ ማህበረሰብ መገንባት ትችላላችሁ።
- ኦግመንትድ ሪያሊቲ ፊልተርስ የተለያዩ ፌስ ፊልተር አፕሊኬሽኖች ሰዎችን ለማስተማር እና ለማነሳሳት በማህበራዊ መድረኮች ላይ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ጥያቄዎች፣ ጨዋታዎች፣ ወዘተ አሏቸው።

**ጠቃሚ ምክር:** ጥበባዊ ስራዎችን ከቴክኖሎጂ ጋር በማጣመር የስቶሪቴሊንግ ዲጂታል መጽሐፍትን በመስራት አንባቢዎች ምርጫቸውን በመግለጽ እንዲያነቡ ማረግ ትችላላችሁ። ይህ ማለት ተጠቃሚዎች የሚፈልጉትን የታሪኩ ሴራ በመምረጥ እናንተ ከነደፋችሁት ኢሉስትሬሽኖች መምረጥ ይችላሉ።

**ጠቃሚ ምክር:** በሙስና ላይ አጫጭር ጨዋታ ስለመንደፍስ

ይህ ዓይነቱ ፈጠራ ተሳትፎን ይጨምራል። እርግጥ ነው ያላችሁ የፋይናንስ ሀብቶች ማድረግ የምትችሉትን ሊገድቡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ከላይ ባየነው ክፍል ውስጥ ብዙ ወጪ የማይጠይቁ ብዙ አማራጮች አሉ።

ለማጠቃለል ያህል ፈጠራ እና ኢኖቬሽን ማለት ጥበብን እና ቴክኖሎጂን መጠቀም ብቻ እንዳልሆነ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ችግርን ለመፍታት ፈጠራዊ እና ኢኖቬቲቭ ለመሆን ብዙ መንገዶች አሉ። ሌሎችን ለማነሳሳት እና ለማስተማር ተጨማሪ ምሳሌዎች በክፍል ዘጠኝ እንመለከታለን።



ምሳሌ: ኦግመንትድ ሪያሊቲ እና ቴክኖሎጂ መስተጋብር።




A Choose Your Own Adventure series book and an e-book by Edward Packard.

# 06: አጋሮችን አግኙ

ተፅዕኖን ከፍ ለማድረግ እና ውጤቶችን ለማምጣት በጋራ መስራት መሠረታዊ ነው። ሙስናን መከላከል እና መዋጋት በአንድ ሰው ብቻ ሊከናወን አይችልም። ሙስናን ለመዋጋት ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰቦች እና ድርጅቶች እንዲሁም በመንግስትና በግሉ ዘርፍ የሚደረጉ ጥረቶች ያስፈልጋሉ። ይህ የጋራ ጥረት ተጽዕኖን ያጎለብታል፣ ድርጊቶችን ያጠናክራል፣ እንዲሁም በማህበረሰባችሁ እና ከዚያም በላይ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ አቀራረብን ያበረታታል። ስለዚህ አጋሮችን ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነው። እነዚህን ባለድርሻ አካላት መለየትና ማግኘት፤ እውቀታችሁን ማሳደግ፣ አቅማችሁን ማጠናከር እና ድጋፍ ማግኘት በጣም አስፈላጎ እርምጃዎች ናቸው።


የመጀመርያ እርምጃ ሊሆን የሚገባው የባለድርሻ አካላት መፈለኛ ማጥናት ነው። ከክፍል ሶስት ጋር በተያያዘ (ኢኒሼቲቫችሁን አውድ ውስጥ በማድረግ) ይህንን አስቀድማችሁ አከናውናችሁት ሊሆን ይችላል። ካልሆነ ግን ከናንተ ጋር ሊሰሩ የሚችሉ የባለድርሻ አካላትን ዳሰሳ ያዘጋጁ። የኢኒሼቲቫችሁን ግቦች ለማሳካት የሚረዷችሁ ቁልፍ ተዋናዮች እነማን እንደሆኑ ወይም በተቃራኒው ለውጥ የማምጣት እድሎቻችሁን ሊቀንሱ የሚችሉት እነማን እንደሆኑ ይለዩ። ይህን በማድረግ ለውጥን ለማምጣት ትኩረት ልትሰጧቸው የሚገቡ ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን ለመለየት ይረዳችኋል።

የባለድርሻ አካላት ዳሰሳ ከሰሩ በኋላ አንዳንድ ባለድርሻ አካላትን ማግኘት፣ ወዳጅነት መፍጠር እና ጥምረት መገንባት ይጀምሩ።

### ለኢኒሼቲቫችሁ ከፍተኛ ደረጃ ድጋፍ ማግኘት

ለአንዳንድ ስራዎቻችሁ ከታዋቂ፣ ከታመኑ እና ከተከበሩ ዝነኛ ሰዎች ጋር አጋርነት መፍጠር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይህ በተለያዩ ማህበረሰቦችና አገሮች ውስጥ የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ቢችልም በአጠቃላይ በሮችን ለመክፈት እና ለውጥን በፍጥነት ለማምጣት ይረዳል።

ለምሳሌ ያክል የፓርላማ አባላት፣ የከተማ ከንቲባዎች ወይም የሃይማኖት መሪዎችን በክልል ወይም በብሔራዊ ደረጃ የፀረ-ሙስና ሻምፒዮን ማድረግ ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ እንደ ኢኒሼቲቫችሁ ዓይነት መሠረት አስተማሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች፣ ወይም የወላጅ-መምህር ማህበር መሪዎች ወይም ተወካዮች ፋሲሊቴተር እና ደጋፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ቀደም ብለን እንደገለጽነው ሙስና ሁሉንም ሰው ይጎዳል። ስለዚህ በሙስና የተጎዱ እንዲሁም በተመሳሳይ ኢኒሼቲቭ እየሰሩ ያሉ ሰዎችን ማግኘት ትችላላችሁ።



### ኢኒሼቲቫችሁን ለመንደፍ እና ለመተግበር አጋሮችን እና የቡድን አባላትን ማግኘት

በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ወጣቶች በሙስና ተሰላችተዋል፤ እናም ብዙዎቹም በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ነገር ለማድረግ እየሞከሩ ነው። በማህበረሰባችሁ፣ በክልላችሁ፣ በአገራችሁ (እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ) አጋሮችን ማግኘት ዓላማችሁን ለማጉላት፣ ፈጠራን እና ልዩነትን ለማዳበር፣ እንዲሁም ተጨማሪ ሀብቶችን ለማምጣት ይረዳል። በጣም ቀላሉ እርምጃ ጓደኞቻችሁን እና ቤተሰባችሁን ማሳተፍ ነው። ነገር ግን በማህበረሰባችሁ ወይም በክልላችሁ ውስጥ ካሉ ሌሎች የወጣት ቡድኖች ጋር ህብረት መፍጠርም ጥሩ እርምጃ ነው። አብራቸሁ በምሰሩበት ጊዜ ሃሳቦቻችሁን እና አላማችሁን በግልጽ ማካፈላችሁን እና በበለጠ ለመወያየት አዝውትሮ መገናኘታችሁም የበለጠ እንድትስሩ ያግዛችሁዋል። ሃሳቦቻችሁን ለማጎልበት ጠቃሚ እውቀት፣ ክህሎት እና የተለያዩ አመለካከቶች እንዲኖራችሁ ይመከራል።

### ከሌሎች ስለምመማር

"ዶንት ሪኢንቬንት ዘ ዊልስ"! እናንተ ከምጸሩት ነገር ጋር ተመሳሳይ ነገር የሚያደርጉ ወይም ከዚህ በፊት ያደረጉ ሌሎች ወጣቶች ወይም የወጣቶች ቡድኖች መኖራቸውን መፈለግና ማወቅ ይገባችኋል። ከልምዳቸው ለመማር፣ የተደጋጋሚ ሥራን እና ተመሳሳይ ስህተቶችን ከመድገም ለመቆጠብ እነሱን ማግኘት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው።

### ሪሶርሶቻችሁን ለማስፋት ወዳጅነቶችን ይገንቡ

ከሌሎች ጋር አብሮ መስራት ሪሶርሶችን ማስፋትና ማጠናከር ማለት ነው። ውጤታማ እና ዘላቂ ለመሆን ኢኒሼቲቫችሁ የመነሻ የገንዘብ ድጋፍ ሊፈልግ ይችላል። አጋሮችን መፈለግ ነባር ሪሶርሶችን ለመጠቀም ብቻ ሳይሆን የጋራ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ለማካሄድ የሚያስፈልገውን እምነት እና ፍላጎት ለማዳበርም ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል። የገንዘብ ማሰባሰብ በዓላማችሁ የሚያምኑ እና አስተዋፅኦ ለማድረግ ፍላጎት ካላቸው የማህበረሰብ አባላት፣ ጓደኞች እና ቤተሰቦች የግል ልገሳዎችን በመፈለግ ሊከናወን ይችላል። ይሁን እንጂ ያለ ብዙ የገንዘብ አቅምም ብዙ ሥራ ሊሠራ ይችላል። ስለዚህ ቅድሚያ መስጠት ያለባችሁን ፍላጎቶቻችሁን ከገመገማችሁ ቦሃላ እንደአስፈላጊነቱ ገንዘብ ወደማሰባሰብ መግባት ይመከራል።

### ከዚህ በኋላ ዓለም አቀፋዊ መሆን ትችላላችሁ!

ሙስና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማህበረሰቦች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መዋቅሮች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ሰፊ ችግር ሲሆን በተለይም ግሎባል ሳውዝ ሀገራት ላይ ከፍተኛ መዘዝ ያስከትላል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ትስስሮች እየጠነከሩ በሚሄዱበት ዓለም ውስጥ በወንጀል እና ሙስና ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች የህግ ማዕቀፎችን እና የንግድ መሠረተ ልማቶችን የመጠቀም ክህሎታቸውን እያሳደጉ ይሄዳሉ፤ ይህም የጋራ እርምጃ የሚጠይቅ አንገብጋቢ ዓለም አቀፋዊ ፈተና ያደርገዋል።

በአገሮች እና በድርጅቶች መካከል የእውቀት፣ የልምድ እና የሪሶርስ ልውውጥ በማመቻቸት ይህንን ተግዳሮት ለመቋቋም ዓለም አቀፍ ትብብር ወሳኝ ነው። ለወጣት የፀረ-ሙስና ተሟጋቾች የፀረ-ሙስና ጥረታቸውን ለማጉላት እና ትርጉም ያለው ተጽእኖ ለመፍጠር ዓለም አቀፍ የትብብር ኔትወርኮችን መጠቀም አስፈላጊ ነው። የተማራችሁትን በማካፈል ከኢኒሼቲቫችሁ ጋር የተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮችን ወደ ዓለም አቀፍ መድረኮች ማምጣት ትችላላችሁ። ይህንን ማድረግ የምትችሉት በሚከተሉት መንገዶች ነው፦

- ብሔራዊ የህግ ማዕቀፎችን ለማጠናከር እና ታማኝነትን ለማሳደግ የሚረዱ ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ስታንዳርዶችን እና ምርጥ ልምዶችን (best practives) መቀበልን ማበረታታት።
- በወጣቶች የሚመሩ ኢኒሼቲቮችን ውጤታማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ ሪሶርሶችን፣ እውቀቶችን እና ድጋፎችን ማግኘት።
- ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ የወጣቶች እና ተመሳሳይ አስተሳሰብ ባላቸው ድርጅቶች መካከል ትብብርን መፍጠር፣ ሙስናን ለመዋጋት የተቀናጀ ዓለም አቀፍ ማህበረሰብን ማጠናከር።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዓለም አቀፍ ትብብርን በማጠናከር እና በሀገራዊና ክልላዊ ቡድኖች መካከል ሙስናን ለመዋጋት ያለውን ጠቀሜታ ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ከዓለም አቀፍ ኔትወርኮች ጋር በመሳተፍ እና ኢኒሼቲቮችን ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም ወጣቶች የበለጠ ግልጽ እና ፍትሃዊ ማህበረሰቦችን ለመገንባት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል።

# 07: አካታች ሁኑ

የፀረ-ሙስና ኢኒሺዬቲቭ በምትነድፉበት ጊዜ ሁሉን አቀፍ አካሄድ መከተላችሁን እና በሥርዓተ-ፆታ እና በሰብአዊ መብቶች ላይ የተመሰረቱ አቀራረቦችን መተግበራችሁን አረጋግጡ። ይህ አካሄድ መስቀለኛ (intersectional) መሆን አለበት፤ ማለትም የተለያዩ ማንነቶችንና ተሞክሮዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉንም ቡድኖች በእኩልነት እና ትርጉም ባለው መልኩ ማካተት አለበት።

በሰብአዊ መብቶች ላይ የተመሰረተ የፀረ-ሙስና አካሄድ የመብት ባለቤቶችን (ግለሰቦችን) ማዕከል ያደረጉ ሲሆን ባለግዴታዎችን (መንግስታትን) ደግሞ የሰብአዊ መብት ግዴታዎቻቸውን እንዲያከብሩ፣ እንዲጠብቁ እና እንዲያስፈጽሙ መጠየቅ ነው።

ሙስናን በሥርዓተ-ፆታ እና በሰብአዊ መብቶች ላይ በተመሰረተ አካሄድ መፍታት ውስብስብ መሆኑን እንገነዘባለን። በዚህ ረገድ የUNODC አጭር መመሪያ «Mainstreaming Gender in Corruption Projects/Programmes» ወይም የUNODC ህትመት «The Time is Now: Addressing the Gender Dimensions of Corruption» በማየት መጀመር ትችላላችሁ።

በአጠቃላይ የእነዚህ አቀራረቦች ዋና ዓላማ ፍትሃዊ የዕድል ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ የሕዝብ አገልግሎቶችና ሸቀጦች በእኩልነት እንዲደርሱ ማስቻል፣ እንዲሁም የሰው ልጅ ክብርና ነፃነት ከማንኛውም ዓይነት መድልዎ ነፃ ሆኖ እንዲከበር ማድረግ ነው።

በዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ በፀረ-ሙስና ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን ማካተት ላይ ባወጣው አጭር መመሪያ መሠረት፣ የማንኛውም ጣልቃ ገብነት ዋና ዓላማ የሁሉንም ሰዎች ሕይወት ማሻሻል መሆን አለበት፤ ይህም ሴቶችንና ወንዶችን፣ ልጃገረዶችንና ወንዶች ልጆችን፣ እንዲሁም የተለያዩ የሰውነት ባህሪያት፣ የፆታ ዝንባሌዎች እና የሥርዓተ-ፆታ ማንነቶች ያላቸውን ሰዎች ያካትታል። በመሆኑም ሁሉም ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች የተለያዩ ቡድኖች ያላቸውን ፍላጎት፣ ተሞክሮ እና ተጽዕኖ በግልጽ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባቸዋል።

በተግባር ሙስናን ለመዋጋት እና የሰብአዊ መብቶችን፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና የአካል ጉዳተኞችን ተካታችነት ለማጠናከር የሚከተሉትን ማድረግ ይቻላል፦

- ከእኩዮቻችሁና ከሥራ ባልደረቦቻችሁ ጋር በመተባበር በሙስና፣ በሰብአዊ መብቶች፣ በሥርዓተ-ፆታ እና በአካል ጉዳተኝነት መካከል ያለውን ግንኙነት ግንዛቤ ማሳደግ።
- በተለይም የሙስና ሰለባ የሆኑ ተጋላጭ ቡድኖች ሰብአዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩ እና ውጤታማ ፍትሕና መፍትሔ እንዲያገኙ መደገፍ።
- በተለይም ከሰብአዊ መብቶች ማስከበርና ማስፋፋት ጋር በተያያዘ በየዕለቱ የሚፈጸሙ የሙስና ድርጊቶችን ለመከላከል ግልጸኝነትን፣ ተጠያቂነትን እና የሕዝብ ተሳትፎን ማጠናከር።
- የፀረ-ሙስና የሕግና የተቋማዊ ማዕቀፎችን ከማህበረሰብ ደረጃ ጀምሮ ማጠናከር።
- የሙስናን ሰንሰለት በመስበር ሙስና በሰው ልጅ ሕይወት እና በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያስከትለውን ጎጂ ተጽዕኖ በግልጽ ማሳየት።

አካታችነት ከሰብአዊ መብቶች፣ ከሥርዓተ-ፆታ እና ከአካል ጉዳተኝነት ባሻገር የሚሄድ ሰፊ ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ለምሳሌ የአገሬው ተወላጆችን እይታዎች፣ ፍላጎቶች እና ተሞክሮዎች ከግምት ውስጥ ማስገባትንም ያካትታል። በዚህ ክፍል ግን በአካል ጉዳተኞችን ማካተት ላይ እናተኩራለን፤ ይህም በፀረ-ሙስና ኢኒሺዬቲቫችሁ ውስጥ ብዝሃነትን ለማካተት የፈጠራ አስተሳሰባችሁን ለማነቃቃት ጥሩ መነሻ ይሆናል።

የአካል ጉዳተኞችን ማካተት ማለት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎአቸውን ማረጋገጥ እና የራሳቸውን ውሳኔ የመወሰን አቅማቸውን (agency) ማጠናከር ማለት ነው። አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው የራሳቸውን ፍላጎትና የሚሹትን ነገሮች ከሌሎች በተሻለ ያውቃሉ። ስለዚህ ፍላጎታቸውንና ስጋታቸውን በራሳቸው መግለጽ፣ በሕክምና ውሳኔዎች፣ በአገልግሎት አሰጣጥ እና በገንዘብ አጠቃቀም ጉዳዮች ላይ መማከር እንዲሁም ረዳቶቻቸውን መምረጥና ማስተዳደር መቻል አለባቸው።

የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ዋና መፈክሩ "ያለ እኛ ምንም ነገር የለም" የሚል ነው። ሙስና ሁሉንም ይጎዳል፤ ነገር ግን አካል ጉዳተኞችን የበለጠ ተጋላጭ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ አካል ጉዳተኞች ስለ ሙስና የሚማሩበት፣ ክህሎት የሚያዳብሩበት እና ሙስናን ለመቃወም የሚያስፈልጉ አመለካከቶችን የሚያጎለብቱበት ሁሉን አቀፍና ተደራሽ የመማሪያ አካባቢ መፍጠር ይገባል። በተጨማሪም አካል ጉዳተኞች እንደ የሙስና ሰለባ ያላቸውን ተሞክሮ በመጠቀም በፀረ-ሙስና ጥረቶች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታትና ማስቻል አስፈላጊ ነው።

ይህን ጉዳይ በውጤታማና ሁሉን አቀፍ መንገድ ለመፍታት አካል ጉዳተኞችን ከፀረ-ሙስና ኢኒሺዬቲቫችሁ የእቅድ ዝግጅት መጀመሪያ ጀምሮ ማሳተፍ ወሳኝ ነው። ከአካል ጉዳተኞችና ከሚወክሏቸው ድርጅቶች ጋር በመተባበር ተጨባጭ እውቀትና ልምድ ማግኘት፣ ምክክር እና ስልጠና መውሰድ እንዲሁም በኢኒሽዬቲቩ ትግበራ ውስጥ ንቁ ሚና እንዲኖራቸው ማስቻል ይገባል።

በተጨማሪም ወጣት አካል ጉዳተኞችን በትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ዲዛይን ላይ ከመጀመሪያው ጀምሮ ማሳተፍ፣ በከተማችሁ፣ በአገራችሁ ወይም በክልላችሁ ያሉ የአካል ጉዳተኞች ማህበረሰቦች ለምን ጉዳይ ቅድሚያ እንደሚሰጡ ለመረዳት ጠቃሚ ዕድል ይፈጥራል። ይህም ኢኒሺዬቲቫችሁ ከተጨባጭ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ያግዛል።

በተጨማሪ የሚሳተፉ አካል ጉዳተኞች ከሌሎች አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ተሳታፊዎች ጋር በጋራ እንዲማሩና እንዲለዋወጡ የሚያስችል የትምህርት አካባቢ መፍጠር ይመከራል። ይህ እርስ በርስ መከባበርን ያጠናክራል፤ ለሁሉም ተሳታፊዎች ጠቃሚ በጋራ የመማር ልምድ ይፈጥራል። ይህ መርህ በፀረ-ሙስና ትምህርት፣ በሲቪክ ተሳትፎ እና በሌሎች ተዛማጅ ፕሮግራሞች ሁሉ ሊተገበር ይገባል።

የአካል ጉዳተኞችን ማካተት ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር፣ ዘላቂ ልማትን ለማሳካት፣ እንዲሁም ሰላምና ደህንነትን ለማጠናከር ወሳኝ ነው። የተባበሩት መንግስታት የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳ ያስቀመጠውን "ማንንም ወደ ኋላ አለመተው" የሚለውን መርህ በተግባር ማስፈጸም ይጠበቅብናል። ይህም ከአካል ጉዳተኞች ጋር በመተባበር እና ፍላጎቶቻቸውን በማዕከል በማድረግ መሥራትን ያካትታል። በዚህ መንገድ ብቻ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተግባር መጠበቅና ማጠናከር፣ ፍትሃዊና አካታች ማህበረሰብ መገንባት፣ እንዲሁም ለሁሉም ሰው ሙስናን የመቋቋም የተሻለ የወደፊት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።

በመቀጠል የቀረበው አካል ጉዳተኞችን በሚያካትት መልኩ የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭን ለማቀድና ለመተግበር እንደ መመሪያ ሊያገለግል ይችላል።

### አንድን ፕሮግራም ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽና አካታች እንዴት ማድረግ ይቻላል?

አካል ጉዳተኞች በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴዎች ላይ በእኩልነት እንዲሳተፉና አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ አካታች፣ ተደራሽ እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ መፍጠር አስፈላጊ ነው። ይህን ለማሳካት ጥሩ ዝግጅት፣ ቅድመ እቅድ እና ግልጽ ግንኙነት ወሳኝ ናቸው። የሚከተሉት ቀላል እና ተግባራዊ ምክሮች ይረዳሉ፦

- ለተሳታፊዎች ጥሪዎን ሲያስተውቁ ከአካል ጉዳተኞች ማመልከቻዎችን በግልጽ መጋበዝ እና ሊሰጡዎት የሚችሉትን ማንኛውንም ልዩ እርዳታ እና ድጋፍ ማብራራት እና አመልካቾች ማንኛውንም ልዩ ፍላጎት የሚጠይቁበትን ቦታ መስጠት አስፈላጊ ነው። ብዙ አካል ጉዳተኞች መድልዎ እንደሚደርስባቸው ወይም ፍላጎቶቻቸው የማይሟሉ ከሆነ ከማመልከት መቆጠብ ትችላላችሁ።
- ለተሳታፊዎች ጥሪዎን ከጀመራችሁ በኋላ ስለ ፕሮጀክቱ ለማሳወቅ እና ጥሪያቹን እንድታካፍሉ እና ከማህበረሰባቸው ውስጥ ለሚገኙ ተዛማጅ አውታረ መረቦች እና ተሳታፊ ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎች እንድታሰራጩ ለመጠየቅ ወደ አካል ጉዳተኞች አውታረ መረቦች ወይም ማህበረሰቦች መድረስን ማሰብ ትችላላችሁ።
- የአካል ጉዳተኞች እንደሚገኙ ካወቃችሁ ቦሃላ ልዩ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ሳያስቡ ከእነሱ ጋር ይገናኙ እና ስለ ልዩ ፍላጎቶቻቸው ጠይቋቸው። የምልክት ቋንቋ ትርጓሜ፣ የባለሞያ ባለሙያ፣ የብሬይል ቁሳቁሶች፣ የግል እርዳታ፣ በአካል ተደራሽ የሆነ ቦታ (ለምሳሌ፣ ሊፍት፣ መወጣጫ ወይም መታጠቢያ ቤት) ወይም ቅድመ ዝግጅት እና የገንዘብ ወጪ የሚጠይቅ ሌላ ማንኛውም እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው አስቀድመው እወቁ። ከተመጣጣኝ ፍላጎቶች ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ለመሸፈን የአደጋ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ ለመጠየቅ መሞከር ትችላሉ። ገንዘቡ ከሌለዎት፣ ዝቅተኛ ወይም ያለክፍያ አማራጭ እርምጃዎችን ከተሳታፊዎች ጋር ተወያዩ።የመማሪያ እንቅስቃሴዎችን ለሁሉም ተሳታፊዎች ተደራሽ በሆነ መንገድ ያዘጋጁ። የመተዋወቂያ ጨዋታዎች፣ የቡድን ውይይቶች፣ ፊልም ማሳያዎች እና የፈጠራ ስራዎች ሲዘጋጁ የተሳታፊዎችን የተለያዩ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ ያስገቡ። ለምሳሌ ማየት የተሳናቸው ካሉ በእይታ ብቻ የሚመሰረቱ እንቅስቃሴዎችን ያስወግዱ።
- የመማሪያ ተግባሮቹን ሁሉን አቀፍ አድርጉ፡ በእርስ በእርስ መተቃወቅ ወይንም በአይስ ብሬከር እንቅስቃሴዎችን እንድትጀምሩ ይበረታታል። ከዚያም የፊልም ቀረጻዎችን፣ ጭብጥ ያላቸውን ውይይቶችን፣ አሳታፊ የፈጠራ እንቅስቃሴዎችን ወዘተ አስቡ። ይህ የሚጠቅመው ከአካል ጉዳተኞች ተሳታፊዎች ጋር ተጨማሪ የፅንሰ-ሀሳብ ምክክር ከማድረግ ብቻ ተብሎ የታሰበ ነው። ለምሳሌ ማየት የተሳናቸው ሲኖሩ ማየትን እና ፍጥነትን የሚነኩ አይስ ብሬከርሮችን ማቅረብ የመገለል ስሜትን ሊያዳብር ይችላል።
- የስልጠና ቁሳቁሶችን ከስልጠናው በፊት ለተሳታፊዎች አድርሱ። ይህ ማየት የተሳናቸውን ወይም ዝቅተኛ የማየት ችሎታ ያላቸው ሰዎች በስክሪን አንባቢ ሶፍትዌር ተጠቅመው ቀድመው ማጥናት ሊፈልጉ ይችላሉ። ቪዲዮዎች ደግሞ የጽሑፍ መግለጫ (captions) እና አስፈላጊ ሲሆን የድምፅ መግለጫ (audio description) ሊኖራቸው ይገባል።
- አሰልጣኞችና አዘጋጆች ከአካል ጉዳተኞች ጋር የመግባባት መሠረታዊ ሥነ-ምግባር ሊያውቁ ይገባል። ለምሳሌ ማየት የተሳነው ተሳታፊን በስሙ ማነጋገር፣ በስክሪን ላይ የሚታዩ ምስሎችን በቃላት መግለጽ እና ሁሉም ተሳታፊዎች በእኩልነት እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል። የእይታ ይዘት የሚቀርበውን በቃል መግለጽም አስፈላጊ ሲሆን ግለሰቡም ተሳታፊ ሆኖ እንዲሰማው ይረዳል።
- የስልጠና ቦታውን ለሁሉም ተሳታፊዎች ተደራሽ አድርጉ። ያስታውሱ - የሰዎች ምቾት ከዲዛይን ውበት በፊት መታሰብ አለበት። የዊልቼር ተጠቃሚዎች በቀላሉ እንዲንቀሳቀሱ መንገዶችን ከመሰናክሎች ነጻ ያድርጉ፣ እንዲሁም ማየት የተሳናቸውን ቦታውን እንዲለማመዱት አጭር የአቅጣጫ መመሪያ ወይም ጉብኝት ያዘጋጁ።
- በዝግጅቱ ጊዜና ከተጠናቀቀ በኋላ ስለ ተደራሽነት እና ሊደረጉ ስለሚችሉ ማሻሻያዎች አስተያየት ለመቀበል ክፍት ይሁኑ። የአስተያየት ቅጾችም ለሁሉም ተሳታፊዎች ተደራሽ በሆነ ቅርጸት(format) መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡ።

# 08: ደህንነታችሁ የተጠበቀ ይሁን

በአጠቃላይ ሙስና በሚበረታበት ጊዜ ሰብአዊ መብቶች ይዳከማሉ፤ በተቃራኒው የሙስና ደረጃ ዝቅተኛ በሆነበት ጊዜ ደግሞ በሁሉም ሰዎች ዘንድ ሰብአዊ መብቶች የበለጠ ክብር ያገኛሉ። ለምሳሌ በአምነስቲ ኢንተርናሽናል የ2022/23 ሪፖርት መሠረት ከፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ቢያንስ 50 የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች መብታቸው የተጣሰባቸው ጉዳዮች ተመዝግበዋል[27]። በተጨማሪም በ2022 የFront Line Defenders ዓለም አቀፍ ትንተና መሠረት ከ26 አገራት የተውጣጡ 401 የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች መገደላቸው ተመዝግቧል፤ ከእነዚህ ውስጥ ቢያንስ 15 ጉዳዮች ሙስናን በመቃወማቸው ግለሰቦችን በወንጀል ከመፈረጅ ጋር የተያያዙ ናቸው። እንደ አለመታደል ሆኖ ብዙ የፀረ-ሙስና ተሟጋቾች በሙስናና በሌሎች ወንጀሎች ውስጥ በተሳተፉ ቡድኖች ክትትል ይደረግባቸዋል፤ እንዲሁም የእስር፣ የስም ማጥፋት፣ የዛቻ፣ የትንኮሳ፣ የጭቆና፣ እና የግድያ ሰለባ የመሆን እድል ሁሌም ይኖራቸዋል።

ስለዚህ በምትገኙበት አካባቢ ከፀረ-ሙስና ተሳትፎ አንፃር ያለውን አውድ መረዳት፣ እንዲሁም አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ግላዊ እና ሙያዊ ደህንነታችሁን እና የምትወዷቸውን ሰዎች ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ እርምጃ መውሰድ ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው።

በዚህ ረገድ በጣም አስፈላጊው ምክር እናንተን የሚጠብቁትን ሕጎች ማወቅ ነው። የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽንን ያፀደቁ አገራት የሙስና ሰለባዎችን ለመጠበቅ እና ሙስናን ሪፖርት የሚያደርጉ ግለሰቦችን (ለምሳሌ መረጃ ሰጪዎችን) ለመጠበቅ የተደነገጉትን የኮንቬንሽኑን አንቀጽ 33 እና 34 ተግባራዊ ለማድረግ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ብሔራዊ ሕጎቻችሁን እና በአገራችሁ ውስጥ ባሉ የፀረ-ሙስና ባለስልጣናት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚሰጡትን የሕግ ምክርና ጥበቃ ይመልከቱ (ለምሳሌ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የሕግ ምክርና የተሟጋች ማዕከላት፣ የሪፖርት ማቅረቢያ ቻናሎች፣ የፕሮ-ቦኖ ጠበቆች ኔትወርኮች፣ እንዲሁም በአፍሪካ ውስጥ መረጃ ሰጪዎችን ለመጠበቅ የሚሰሩ መድረኮች፣ የተመሰጠረ የኢሜይል አገልግሎት እና በደህንነት እንዴት እንደሚሰሩ የሚያስረዱ መመሪያዎችና ድጋፎችን ይመልከቱ)።

በተጨማሪም በፀረ-ሙስና ሥራ ውስጥ ያላችሁን ተሳትፎ ለቤተሰባችሁ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ጋዜጠኞችንና ጠበቆችን ጨምሮ በሲቪል ነፃነቶች ጥበቃ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎችን ያካተተ የድጋፍ መረብ መገንባት ይመከራል። እንደ ግለሰብ ብቻችሁን ሆናችሁ ከመንቀሳቀስ ወይም ኢኒሺዬቲቮችን ከመተግበር ይቆጠቡ። ከዚህ ይልቅ ሙስናን የሚቃወሙ ተዋናዮች ጋር በቡድን በመሆን ይስሩ። የጋራ እርምጃ ማለት የሙስና ተዋናዮች የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎችን ለመቃወም ወይም ለማደናቀፍ የሚያወጡትን ወጪ ከፍ ማድረግ ማለት ነው።



# 09: ሌሎችን አስተምሩ

አሁን ጥናታችሁን አድርጋችኋል፤ ስትራቴጂያችሁንም አውጥታችኋል። አሁን ልምዳችሁንና የተማራችሁትን ሌሎችን ለማስተማር ዝግጁ ናችሁ።

ኢኒሼቲቫችሁ የኮሚውኒኬሽን ወይም የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ ከሆነ በተለይ ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ ናችሁ። ስለ ሙስና እና ስለ አሉታዊ ተፅእኖው ግንዛቤ ማስጨበጥ የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁ ዋና ግብ ካልሆነም ሌሎችን ማስተማር አሁንም የኢኒሼቲቫችሁ አስፈላጊ አካል መሆን አለበት።

ለአቀራረባችሁ እና ለምትሰሩት ስራዎች አብሮነትን ማጠናከር እና ድጋፍ መገንባት አስፈላጊ ነው። ስለ ኢኒሼቲቫችሁ ግንዛቤን ለማሳደግ እና ተሳትፎን ለማበረታታት ስልታችሁን ለባለድርሻ አካላት፣ ለእኩዮች፣ ለሥራ ባልደረቦች፣ ለጓደኞች እና ለቤተሰብ አባላት አቅርቡ።

ሁሌም ቢሆን ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ መንገድ ሃሳቦቻችሁን ግለጹ። ድጋፍን ለማግኘት ታዳሚዮቻችሁን ስለ ኢኒሼቲቫችሁ ግቦች እና ሙስናን ለመዋጋት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ማሳመን ያስፈልጋችኋል። ባለድርሻ አካላት ኢኒሼቲቫችሁን እንዲደግፉ ለማበረታታት ጥናት የተደረገባቸው እይታዎችን፣ አሳማኝ ኬዝ ስተዲዎችን፣ እውነታዎችን እና ማስረጃዎችን ይጠቀሙ። በፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁ ውስጥ ፈጠራን እና ኢኖቬሽንን እንዴት ማካተት እንደምትችሉ ሀሳቦችን እና ምክሮችን ለማግኘት ክፍል አምስትን ተመልከቱ።

ኢኒሼቲቫችሁን በገንዘብ የሚደግፉ እና በሥራችሁ ውስጥ የሚሳተፉ ወይም የሚተባበሩ ሰዎችን ዘወትር የደረሳችሁባቸውን ግኝቶች በመስጠት እና አስተያየት ለመቀበል ዝግጁ መሆናችሁን አስታውሱ። ኢኒሼቲቫችሁን በምታስቀጥሉበት ጊዜ ባለድርሻ አካላትን በሂደቱ ውስጥ ማቆየት አስፈላጊ ነው። ስለ ኢኒሼቲቫችሁ መደበኛ አፕዴቶችን እንዲሁም ስኬቶቻችሁን ማጋራታችሁን አትዘንጉ።

---

[27] Amnesty International, Amnesty International Report 2022/23 (London, 2023).

# 10: ይተግብሩ!

የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁን ለመጀመር እና ተግባራዊ ለማድረግ ጊዜው አሁን ነው!

ይህ ክፍል ትልቅ ለውጥ ያመጡና እና ገድሞ ለመስራት ቀላል የሆኑ የተሳኩ የኢኒሼቲቭ ምሳሌዎችን እናቀርብላቹሃለን። መረጃው ለፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁ እውቀት እና መነሳሻ ይሰጣችኋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። አሁንም ማስታወስ ያለብን ነገር ይህ የተሟላ ዝርዝር አይደለም፤ እዚህ ያልተካተቱ ብዙ ተጨማሪ ምሳሌዎች አሉ።

በዓለም ዙሪያ ያሉ የትምህርት ተቋማት ሙስናን ለመግለጥ፣ ለማውገዝ እና ለመዋጋት እንዲሁም ታማኝነትን፣ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን እንደ መሰረታዊ ማህበራዊ እሴቶች ለማሳደግ የሚረዱ መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ላይ ናቸው። በፖርቱጋል የሚገኘው የRedEscolas ፀረ-ሙስና ፕሮግራም አንዱ ምሳሌ ነው። ይህም በትምህርት ቤታችሁ፣ በዩኒቨርሲቲያችሁ ወይም በማህበረሰባችሁ ውስጥ የራሳችሁን ኔትወርክ ለመፍጠር እንደ መነሳሻ ሊያገለግል ይችላል። ፕሮግራሙ በAll4Integrity እየተዘጋጀ ሲሆን ሦስተኛው የፕሮግራሙ ዙር በአሁኑ ጊዜ (ከ2023 እስከ 2024) በሂደት ላይ ነው። 59 ትምህርት ቤቶችን (50 ከፖርቱጋል እና 9 ደግሞ ከአንጎላ፣ ብራዚል፣ ቻይና፣ ፈረንሳይ እና ሞዛምቢክ) ያካትታል።

ዋናው ዓላማ በወጣቶች መካከል የጋራ ቦታና የጋራ ጥቅም (public space and common good) ስሜትን እንዲሁም በአካባቢ እና በማዕከላዊ ተቋማት ላይ ያለውን መተማመን እና ርህራሄ ማሳደግ ነው። ይህም ግንዛቤን በማስጨበጥ እና በሀገሪቱ ውስጥ የታማኝነት ባህልን ለማጠናከር የሚያግዙ ባህሪያትን በመቀየር የሚከናወን ሂደት ነው። ማንኛውም ትምህርት ቤት ወጣቶች ተዋናዮች እና የለውጥ አንቀሳቃሾች እንዲሆኑ በመርዳት ለፕሮግራሙ ማመልከት ይችላል። በእነዚህ ጥረቶች ውስጥ በመሳተፍ ትምህርት ቤቶች "ዲጂታል ሲል" እና "የፀረ-ሙስና አምባሳደር" የምስክር ወረቀት ሊያገኙ ይችላሉ።



የቀይ ሬድስኮላስ ፀረ-ሙስና ፕሮግራሞች በፖርቱጋል የ2ኛው የሬድኤስኮላስ የመጨረሻ ሥነ ሥርዓት ጁን 8፣ 2023

### ሙስናን በመዋጋት ረገድ የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሚና ለማጠናከር የፍኖተ ካርታ

የYouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ አባላት ከሌሎች ወጣቶች ጋር በመሆን በተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን ተግባራዊነት ረገድ የመንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮችን ሚና እንዴት ማጠናከር እንደሚቻል በሚመለከት በእስያ፣ በአውሮፓ እና በደቡብ አሜሪካ ከሚገኙ የመንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች ጋር በተካሄደ የአንድ ዓመት የምክክር ሂደት ውስጥ ተሳትፈዋል።

የዚህ ሂደት ውጤት በዓይነቱ የመጀመሪያው የወጣቶች መግለጫ እና በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜቲካ መንግስት የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ (ሪኮመንዴሽን) ነበር። ይህ የውሳኔ ሃሳብ የመንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮችን (ወጣቶችን፣ የአካዳሚክ ተቋማትን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን) ሙስናን በመዋጋት ረገድ ለማጠናከር የተዘጋጀ የፍኖተ ካርታ ሲሆን በዓይነቱም የመጀመሪያው ነው። ይህ የፍኖተ ካርታ በታህሳስ 2023 በአትላንታ ዩናይትድ ስቴትስ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን አባል ሀገራት ኮንፈረንስ ላይ ቀርቧል። [28]

### በኢንዶኔዥያ ‹‹እኔ ሙስናን የሚቃወም ሴት ነኝ›› ኢኒሼቲቭ

እ.ኤ.አ. በ2014 በኢንዶኔዥያ የሚገኘው የሙስና ማጥፋት ኮሚሽን እና የአውስትራሊያ መንግስት በመተባበር በኢንዶኔዥያ "ሳያ ፔሬምፑን አንቲኮሩፕሲ" ("እኔ ሙስናን የምቃወም ሴት ነኝ") የተሰኘ ኢኒሼቲቭ ጀምረዋል።

እ.ኤ.አ. በ2012 የፀረ-ሙስና ኮሚሽኑ ባደረገው ጥናት አባቶች ለልጆቻቸው ስለ ታማኝነት የሚያስተምሩት አራት በመቶ ብቻ መሆናቸውን አረጋግጧል። ጥናቱ በተጨማሪም እናቶች ለልጆች የሞራልና ትምህርት ዋና ምንጭ መሆናቸውን አሳይቷል። በዚህ የዳሰሳ ጥናት ውጤት መሠረት ኢኒሼቲቭ የተቋቋመ ሲሆን 25 ሴቶችን (እናቶችን፣ አስተማሪዎችን እና ሴት አክቲቪስቶችን) በፀረ-ሙስና ትምህርት ለማሰልጠን እና ይህንንም ትምህርት እንዲያስፋፉ ዓላማ ተይዞለታል። የፕሮጀክቱ ወሰን በመቀጠል እየሰፋ ሲሄድ ሴቶችን በሕግ አስከባሪ አካላት እና በሌሎች ዘመናዊና ባህላዊ ሙያዎች ውስጥ በማካተት በሥራ ተቋማቸው ውስጥ ያለውን የሙስና ችግር በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት የሚያስፈልጉ ማሻሻያዎችን የመለየት ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። እስካሁን ድረስ ኢኒሼቲቭ ወደ 1,600 የሚጠጉ ተሳታፊዎችን ያሳተፈ ሲሆን በኢንዶኔዥያ ያሉትን 34 ግዛቶች ሸፍንዋል።

ኢኒሼቲቭ ስኬት እና ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ አዳዲስ ዘዴዎች በኢንዶኔዥያ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች እውቅና አግኝተዋል። እነዚህ ዘዴዎች የፀረ-ሙስና እሴቶችን፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ለማስተዋወቅ ጌሚፊኬሽንን መጠቀምን ያካትታሉ። በዚህም ሂደት ኢኒሼቲቭ ሴቶች ሙስናን ለመዋጋት የሚያስችል ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኗል።

[28] See the website of the tenth session of the Conference of the States Parties to the United Nations Convention against Corruption, available at www.unodc.org/unodc/corruption/COSP/session10.html.

[29] UNODC, Independent Commission Against Corruption and International Association of Anti-Corruption Authorities, Policy Guide for National Anti-Corruption Authorities on Meaningful Youth Engagement in Anti-Corruption Work (2023).



### በፀረ-ሙስና ሥራ ላይ ትርጉም ያለው የወጣቶች ተሳትፎን (meaningful youth engagement) በተመለከተ ለብሔራዊ የፀረ-ሙስና ባለሥልጣናት የፖሊሲ መመሪያ

ኢንዲፔንደንት ኮሚሽን ፎር አንቲ ኮራፕሽን (ICAC)፣ ዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ እና የዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ባለሥልጣናት ማህበር የፀረ-ሙስና ባለሥልጣናት ወጣቶችን ፀረ-ሙስና ላይ ትርጉም ባለው መንገድ እንዲሳተፉ የሚያግዝ የፖሊሲ መመሪያ አዘጋጅተዋል።[29]

የYouthLED ኢንቴግሪቲ አማካሪ ቦርድ አባላት እና የICAC አምባሳደሮች ፕሮግራም አባላት በመመሪያው ዝግጅት ሂደት ውስጥ ተሳትፈዋል። ይዘቱንና አወቃቀሩን ለመቅረጽ ወጣቶች መሳተፋቸው እንዲሁም ግብረመልስና ሀሳቦችን በመስጠት ይህ በፀረ-ሙስና ሥራ ውስጥ ትርጉም ያለው የወጣቶች ተሳትፎ ጥሩ ምሳሌ ነው።

### በፓኪስታን ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች የመረጃ ነፃነት ሕጎችን ተደራሽ ማድረግ

እ.ኤ.አ. በ2019 መንግሥታዊ ያልሆነው ድርጅት ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ፓኪስታን የመረጃ፣ የአገልግሎት እና የግብአት ተደራሽነትን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ለአካል ጉዳተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ አካሂዷል። በመቀጠልም በቶባ ቴክ ሲንግ አውራጃ ውስጥ ከ60 በላይ አካል ጉዳተኞች የአካል ጉዳት የምስክር ወረቀቶችን ለማግኘት የመረጃ ነፃነት መብታቸውን ተጠቅመዋል።

### በናይጄሪያ አካል ጉዳተኞች ሙስናን እንዲዋጉ ማገዝ

በናይጄሪያ የሚገኘው የአካል ጉዳተኞች ማዕከል ከአክሽን ኤይድ፣ ከዩኬ ኤይድ እና በካዱና፣ ካኖ እና ሌጎስ ግዛቶች ከሚገኘው የኮሙኒኬሽን እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ማዕከል ጋር በመተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮጀክት አካሂዷል።[30] የፕሮጀክቱ ዓላማ አካል ጉዳተኞችን ለሙስና የበለጠ ተጋላጥ እንደሆኑ የሚያስረዳ፣ በተለይም ከጤና አጠባበቅ፣ ከትምህርት እና ከሌሎች አገልግሎቶች ያላቸው መብቶች ጋር በተያያዘ ማስተማር ነበር።

ሌላው የፕሮጀክቱ ዓላማ አካል ጉዳተኞች ብቁ ሊሆኑ እና የሚገባቸውን ጥቅማጥቅሞች ለማሳወቅና መረጃ ለመስጠት የሚመለከታቸውን የመንግሥት ፕሮግራሞች መከታተል ነበር። ማዕከሉ በመንግሥት ዘርፍ ውስጥ ስላለው ሙስና ቅሬታ እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል ለአካል ጉዳተኞች ስልጠና ሰጥቷል።

### የወንጀል ሰለባ ለሆኑ አካል ጉዳተኞች መሳሪያዎች

በአውሮፓ ህብረት ውስጥ የሚሠራው መንግሥታዊ ያልሆነው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት Validity የወንጀል ሰለባ የሆኑ አካል ጉዳተኞች በወንጀል ፍትህ ሂደቶች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ለመርዳት ተግባራዊ መሳሪያዎችን እያዘጋጀ ነው።[31]

### በጣሊያን ውስጥ የሲቪክ ክትትል

ከ2016 ጀምሮ ግሩፖ አቤሌ ኤንድ ሊቤራ በጣሊያን ውስጥ በማህበረሰቦቻቸው ውስጥ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለመከታተል እና ለውጥ ለማምጣት የሚፈልጉ ወጣቶችን ተግባራት ሲደግፉ ቆይተዋል።

ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2018 አንድ የወጣቶች ቡድን ጣሊያን ውስጥ በኤርቤ የአካባቢውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ አድርጓል። ይህም በአካባቢው የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች መኖራቸውን በተመለከተ ግንዛቤን ለማሳደግ ረድቷል። ከቃለ መጠይቁ በኋላ ወጣቶቹ ከተደራጁ የወንጀል ቡድኖች የተወረሱ ንብረቶችን (በብስክሌት) ጎብኝተው ለማህበረሰብ ጥቅም እንዲውሉ ጠይቀዋል።[32]

ግሩፖ አቤሌ ኤንድ ሊቤራ “You Monitor” የተሰኘ የአውሮፓ ፕሮጀክት አጋሮች ናቸው። የYou Monitor Toolkitን ይመልከቱ፤ ይህ ቱልኪት ለሞኒተሪንግ ሥራ ደረጃ በደረጃ መመሪያ የሚሰጥ ሲሆን በተለያዩ ቋንቋዎችም ይገኛል።

### MoMoEU በአውሮፓ ህብረት ውስጥ ተጨማሪ የሞኒተሪንግ እርምጃ

የ “MoMoEU: More Monitoring action in the EU” ፕሮጀክት በስምንት የአውሮፓ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተመሠረተ ሲሆን ቀላል ማብራሪያዎችን፣ የፕሮጀክት ሀሳቦችን እና ዲጂታል ግብዓቶችን (ሁለት ጨዋታዎችን ጨምሮ) የሚያቀርብ የሲቪክ ሞኒተሪንግ ላይ ያተኮረ የትምህርታዊ ድረ-ገጽ ፈጥሯል። ዲጂታል ግብዓቶቹ ከ15 እስከ 25 ዓመት ለሆኑ ወጣቶች የተነደፉ ሲሆን ወደ ሰባት ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። በድረ-ገጹ ላይ ያሉትን ግብዓቶች ይመልከቱ።

[30] Upright for Nigeria, “Campaign Communication Strategy” (2020)

[31] Validity, “Voices for Justice: Communicating with Victims of Crime with Disabilities”.

[32] Confiscati Bene, “Estate Liberi! - Monitorando Bene, Erbè VR 2018”, YouTube, video, 21 May 2024.

[33] Integrity Action, “Integrity clubs in schools: A how-to guide (according to young people)” (2022).

### የታማኝነት ክበቦች (Integrity Clubs)

ከታማኝነት ክበቦች ጋር ወጣቶች በትምህርት ቤቶቻቸው ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን መከታተል ይችላሉ። እንደየውሃ እና የንፅህና አጠባበቅ ችግሮች፣ የመምህራን እና የተማሪዎች ጠባይ፣ የትምህርት ቤት መገልገያዎች ተደራሽነት እና የመሠረታዊ አቅርቦቶች (ጠረጴዛዎች፣ ጥቁር ሰሌዳዎች፣ ወዘተ) እጥረት የመሳሰሉትን መከታተል ያስችላተዋል። አንዳንድ ክበቦች በማህበረሰባቸው ውስጥ ያሉ አገልግሎቶችን እና የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በመመልከት የስራዎቻቸውብ ወሰን አስፋፍተው ከመማሪያ ክፍላቸው ወጥተው በማህበረሰብ ውስጥ የሚሰሩም አሉ።

እንዲሁም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ላሉ የታማኝነት ክበቦች የታማኝነት እርምጃ መመሪያን መመልከት ትችላላችሁ።[33] በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የተሳካ የታማኝነት ክበብ ለማቋቋም ቅስቀሳ ለማግኘት ይረዳችኋል። ለምሳሌ ሌሎች ወጣቶች በክትትል ሥራዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ማነሳሳት ያስችላቹሃል።

### በሆንዱራስ ሙስና እና ያለመከሰስ መብትን ለመዋጋት የሚደረገውን ትግል የመደገፍ ተልዕኮ

በሆንዱራስ ሙስናን እና ያለመከሰስ መብትን ለመዋጋት የተቋቋመው የድጋፍ ተልዕኮ በአሜሪካ መንግስታት ድርጅት (OAS) እና በሆንዱራስ መንግስት ትብብር የተመሠረተ ሲሆን ዓለም አቀፍ ትብብር እና የፀረ-ሙስና የሕግ ማዕቀፎችን መተግበር ሙስናን በመዋጋት ረገድ ያለውን አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

ተልዕኮው ለትብብር፣ ለቴክኒክ ድጋፍ እና ለአቅም ግንባታ መድረክ በመፍጠር ወጣቶች በፀረ-ሙስና ጥረቶች ውስጥ ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የሚያበረታታ ጠቃሚ ሚና እየተጫወተ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካ አህጉር የተካሄደው የክፍት መንግስት ጥምረት (OAS Alliance for Open Government) የ2015–2017 የግልጽነት እና የዜጎች ተሳትፎ የአመራር ፕሮግራም የዚህ አይነት ጥረት ምሳሌ ነው።

ይህ ፕሮግራም በሆንዱራስ ከመንግስት ተቋማት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ 25 ወጣት መሪዎችን በማሰባሰብ የለውጥ አራማጆች እንዲሆኑ የሚያግዝ አውታረ መረብ ለመፍጠር ያለመ ነበር። ፕሮግራሙ ወጣቶች ስለ ክፍት መንግስት ስረዓት ጉዳዮች እንዲወያዩ፣ ሀሳቦችን እንዲለዋወጡ እና እውቀትና ልምዶችን እንዲጋሩ የሚያስችል የመማሪያ እና የመሳተፊያ ቦታ ፈጥሯል። ይህ ኔትወርክ ከተለያዩ ዘርፎች የተውጣጡ ወጣት መሪዎችን በማገናኘት በሆንዱራስ ውስጥ ሙስናን መከላከል፣ ግልጽነትን ማሳደግ፣ ተጠያቂነትን ማጠናከር እና የዜጎችን ተሳትፎ ማስፋት የሚያስችሉ አዳዲስ ሀሳቦችን አዳብሯል። ስለ ፕሮግራሙ እንቅስቃሴዎች፣ አጋሮች፣ ተሳታፊዎች እና ውጤቶች በOAS የተዘጋጀው “Open Government in the Americas: Impact and Learning Report 2015–2017” ሪፖርት ውስጥ ተጨማሪ መረጃ ይገኛል።

በአጠቃላይ የዚህ ተልዕኮ መመስረት ሙስናን እና ያለመከሰስ መብትን ለመዋጋት ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎች እና ትብብር ያላቸውን ጠቀሜታ ያሳያል። በአሜሪካ መንግስታት ድርጅት፣ በሆንዱራስ መንግስት እና በወጣት ተሟጋቾች መካከል የተፈጠረው ትብብር የበለጠ ውጤታማ የፀረ-ሙስና ጥረቶችን እንዲካሄዱ አስተዋፅዖ አድርጓል። በተጨማሪም ግልጽ፣ ተጠያቂ እና ፍትሃዊ ማህበረሰቦችን ለመገንባት የሚሰሩ የወጣት ለውጥ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ አስፈላጊ ልምድና ድጋፍ ሰጥቷል።

### YOUNGO – የአየር ንብረት ለውጥ የወጣቶች መንግስታዊ ያልሆነ ኔትወርክ

YOUNGO በተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ኮንቬንሽን (UNFCCC) ሂደት ውስጥ የህፃናት እና ወጣቶች ይፋዊ የምርጫ ክልል (constituency) ነው። ይህ ኔትወርክ ከዓለም ዙሪያ የተውጣጡ ንቁ የህፃናት እና የወጣቶች ተሟጋቾችን (እስከ 35 ዓመት ዕድሜ ያሉ) እንዲሁም የወጣቶች ድርጅቶችን በማሰባሰብ የተመሰረተ ነው።

YOUNGO የወጣቶችን ተሳትፎ በማጠናከር የአየር ንብረት ፖሊሲዎችን በመቅረጽ ሂደት ላይ የወጣቶች አስተያየትና አመለካከት እንዲካተት ይሰራል። በተጨማሪም ወጣቶች በUNFCCC ሂደቶች ውስጥ ድምፃቸውን በይፋ እንዲያሰሙ እና ለአየር ንብረት ፍትህ እና ዘላቂ ልማት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ እንዲያሳድጉ ያበረታታል።

YOUNGO በሚከተሉት ዋና ዋና ዘርፎች ላይ ያተኩራል፦

- ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ እውቀት ማስፋፋት እና አቅም ግንባታ
- ትብብር፣ አጋርነት እና ኔትወርክ ግንባታ
- የፖሊሲ ተሳትፎ፣ ተሟጋችነት እና የውሳኔ ሂደት ላይ ተፅዕኖ ማድረግ
- የወጣቶች ተግባራዊ እርምጃ እና ተነሳሽነት

### ለ UNEP የህፃናት እና ወጣቶች ዋና ቡድን (Children and Youth Major Group to UNEP)

የህፃናት እና ወጣቶች ዋና ቡድን የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም (UNEP) ይፋዊ የወጣቶች ተሳትፎ መድረክ ነው። ቡድኑ በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ ጉባኤ (UNEA) እና ከUNEP ጋር በተያያዙ ሌሎች የአካባቢ አስተዳደር ሂደቶች ውስጥ የወጣቶች ድምፅ እንዲወከል ያደርጋል።

ቡድኑ ከተለያዩ ክልሎች፣ ባህሎች እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራዎች የተውጣጡ ወጣቶችን በማሰባሰብ በአካባቢ ጥበቃ እና በዘላቂ ልማት ጉዳዮች ላይ የወጣቶች ተሳትፎን ያጠናክራል።

በአካባቢ ጥበቃ እና በአካባቢ አስተዳደር ዘርፍ የወጣቶችን ሀሳብ፣ ፈጠራ እና ተሳትፎ በክልላዊ፣ ብሔራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ደረጃ ለማሳደግ ይሰራል።

### የውሃና የአየር ንብረት ዓለም አቀፍ የወጣቶች ህብረት (United International Federation of Youth for Water and Climate)

የውሃና የአየር ንብረት ዓለም አቀፍ የወጣቶች ህብረት በዓለም አቀፍ የሚቲዮሮሎጂ ድርጅት በሚመራው የውሃና የአየር ንብረት ጥምረት (Water and Climate Coalition) ውስጥ የወጣቶችን ድምፅ በይፋ የሚወክል አካል ነው። ዋና ተልዕኮው ወጣቶች በውሃና በአየር ንብረት ፖሊሲዎችና ውሳኔዎች ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማበረታታት ነው። ህብረቱ በውሃና በአየር ንብረት ትምህርት፣ በአቅም ግንባታ፣ በአለም አቀፍ ትብብር፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ በንቃት መሳተፍ እና ሀብት በማሰባሰብ ላይ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማጠናከር ይሰራል። በውሃ ዘርፍ ሙስና በቀላሉ ሊከሰትባቸው ከሚችሉ ዘርፎች አንዱ በመሆኑ የወጣቶች ተሳትፎ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን እና ፍትሃዊ አገልግሎትን ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

### Coding4Integrity ሃካቶኖች

የቴክኖሎጂ ፍላጎት ወይም የኮዲንግ ችሎታ አላችሁ? ከሆነ ዲጂታል ፈጠራን በመጠቀም ሙስናን ለመከላከልና ለማህበራዊ ለውጥ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚያስችላችሁን እድል ተመልከቱ። የዩ.ኤን.ኦ.ዲ.ሲ Coding4Integrity የወጣቶች ፀረ-ሙስና ሃካቶን ፕሮግራም በዚህ መንገድ ጥሩ መነሳሻ ሊሆናችሁ ይችላል።

Coding4Integrity ወጣት ሶፍትዌር ዴቬሎፐሮችን የቴክኖሎጂ አድናቂዎችን ስለ ሙስና፣ ስለ የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን እና ቴክኖሎጂ ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት እንዴት ሊያግዝ እንደሚችል ለማስተዋወቅ የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው። በተጨማሪም ወጣቶች በፀረ-ሙስና ጥረቶች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያበረታታ አዳዲስ ቴክኖሎጂያዊ መፍትሄዎችን እንዲያቀርቡ ያበረታታል።

ተሳታፊዎች በእውነተኛ የሙስና ተግዳሮቶች ላይ የተመሰረቱ የቴክኖሎጂ መፍትሄዎችን የመንደፍና የማቅረብ እድል ያገኛሉ።

በሃካቶኑ ወቅት ወጣት የፈጠራ ባለሙያዎች ከUNODC ባለሙያዎች፣ ከብሔራዊ ፀረ-ሙስና ተቋማት ተወካዮች እና ከቴክኖሎጂ ዘርፍ ባለሙያዎች በቀጥታ ይማራሉ። በተጨማሪም ከኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያዎችና አጋር ድርጅቶች ጋር በሚደረገው ትብብር የቴክኒክ ምክር፣ የመሪነት ድጋፍ እና ሙያዊ ኔትወርክ የመገንባት እድል ያገኛሉ።

ስለወደፊቱ Coding4Integrity ሃካቶን ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት የGRACE ኢኒሼቲቭ ድህረገጽን በቅርብ ይከታተሉ። ከዚህም በላይ እርምጃ መውሰድ ትፈልጋላችሁ? ማህበረሰባችሁ ውስጥ ተመሳሳይ የፈጠራ ውድድር ወይም ሃካቶን ለማዘጋጀት ለምን አትሞክሩም? የለውጥ አካል ለመሆን ራሳችሁን በአዳዲስ ሀሳቦችና ተግባራት ፈትኑ። እንዲህ ዓይነት ኢኒሼቲቮችን ለማደራጀት የሚያስፈልጉትን ሕጋዊ መስፈርቶችና የድርጅት አቋቋም ሂደቶች መረዳት ጠቃሚ ነው። ለዚህም ከሕግ ባለሙያዎች፣ ጠበቆች፣ የሕግ ተማሪዎች እና ነፃ (pro bono) የሕግ ምክር ከሚሰጡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ መፈለግ ትችላላችሁ።

በተጨማሪም በቴክኖሎጂና በፈጠራ ላይ ትኩረት በሚያደርጉ ማህበራዊ ኢንተርፕራይዞች ወይም ስታርትአፖች ውስጥ እንደበጎ ፈቃደኛ መሳተፍ ትችላላችሁ። ይህም ከተለያዩ ፕሮጀክቶች ልምድ እንድታገኙ እንዲሁም የራሳችሁን የፀረ-ሙስና ሀሳብ እንዴት ወደ ተግባር መቀየር እንደምትችሉ እንድትማሩ ያግዛችኋል። እንዲሁም ለደንበኛ ጥበቃ ተቋማት (customer protection agency) (የመንግስትም ሆኑ የግል) አስተዋጽኦ በማድረግ ጠቃሚ ልምድ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም በቴክኖሎጂ ዘርፍ ተፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን እንደ UX ዲዛይን፣ ፕሮግራሚንግ እና የድረ ገጽ ንድፍ (Web Design) ማዳበርም ጠቃሚ ነው።

በመጨረሻም ምንም ዓይነት ኢኒሼቲቭ ብትጀምሩ ከሌሎች ጋር በመተባበር መሥራት ለስኬት ቁልፍ መሆኑን አትዘንጉ። ፈጠራ የሚያድገው በሀሳብ ልውውጥ፣ በትብብር እና በጋራ ሀብት ነው። አንድ ግለሰብ ሀሳብ ሊያፈልቅ፣ ሀብት ሊያሰባስብ፣ ፕሮጀክት ሊጀምር፣ ሊያስተዋውቅ እና ውጤቱን ሊገመግም ቢችልም ይህ በተግባር ብዙ ጊዜ የሚፈጸም አይደለም። የተሳካ ኢኒሼቲቭ ብዙውን ጊዜ የተለያዩ ሚናዎችን የሚያሟሉ ባለድርሻ አካላት በጋራ ሲሰሩ የሚፈጠር ነው። ጠንካራ ሽርክናና የጋራ እርምጃ ለማህበረሰቡ ዘላቂ እና ትርጉም ያለው እሴት ለመፍጠር ከፍተኛ አቅም አላቸውና እነዚህን እድሎች በሚገባ ተጠቀሙ።

### ፌር ፕሌይ: መልዕክት አዘል ሙዚቃ

ፌር ፕሌይ (Fair Play) ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል፣ ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ኮንፈረንስ (IACC) እና JM ኢንተርናሽናል በመተባበር የሚካሄድ ዓለም አቀፍ የሙዚቃ ውድድር ነው። ውድድሩ በሙስና የተጎዱ ሰዎችን ድምፅ ለማሰማት እና ወጣት አርቲስቶች ስለ ታማኝነት፣ ፍትሕ እና ፀረ-ሙስና መልዕክቶቻቸውን በሙዚቃና በሥነ-ጥበብ እንዲገልጹ ዓለም አቀፍ መድረክ ያቀርባል። ከ2010 ጀምሮ ፌር ፕሌይ ከ90 በላይ ሀገራት የተውጣጡ ከ400 በላይ የሙዚቃ ቪዲዮዎችን በማቅረብ ከ10 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ጋር መድረስ ችሏል።

### አርኬዲአ ኧርዝ (Arcadia Earth)

Arcadia Earth በኒውዮርክ ከተማ የሚገኝ የAugmented Reality (AR) ቴክኖሎጂን በመጠቀም ስለ የአየር ንብረት ለውጥ እና ሌሎች የአካባቢ ጉዳዮች ግንዛቤን ለማሳደግ የተዘጋጀ መሳጭ የሥነ-ጥበብ ኤግዚቢሽን ነው። ጎብኚዎች በተለያዩ መሳጭ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች ውስጥ ሲዘዋወሩ የAR መነጽሮችን በመጠቀም ሥራዎቹን በሕይወት




ምንጭ: GRACE initiative.

የተሞሉ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ለምሳሌ 44,000 የፕላስቲክ ከረጢቶችን በመጠቀም የተሰራ አንድ የሥነ-ጥበብ ሥራ በኒውዮርክ የፕላስቲክ ከረጢት እገዳ ከመምጣቱ በፊት በየደቂቃው ይጠቀሙ የነበሩትን የፕላስቲክ ከረጢቶች ብዛት ያሳያል። ይህ ተሞክሮ ተሳታፊዎች ስለ አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች በተግባር እንዲማሩና የራሳቸውን ሚና እንዲያስቡ ያበረታታቸዋል።

### የፀረ-ሙስና ፊልም ፌስቲቫል

የፀረ-ሙስና ፊልም ፌስቲቫል በ2013 በኢንዶኔዥያ የሙስና ማጥፋት ኮሚሽን (KPK)፣ በዩናይትድ ስቴትስ የዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) እና በManagement Systems International (MSI) በመተባበር የተጀመረ ኢኒሼቲቭ ነው። ዓላማው በፊልም ኢንዱስትሪ አማካኝነት የፀረ-ሙስና ግንዛቤን ማሳደግ እና ዜጎችን በተለይም ፊልም ሰሪዎችን፣ ተማሪዎችን እና ተመልካቾችን በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት ነው። ፌስቲቫሉ ተሳታፊዎች ስለ ሙስና፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ታማኝነት የሚያሳዩትን ፊልሞችን እንዲያዘጋጁ በማበረታታት ሥነ-ጥበብ ለማህበራዊ ለውጥ የሚያገለግል ጠንካራ መሣሪያ እንደሆነ ያሳያል።

### ተናገር (Speak Up™)

"ተናገር" (Speak Up™) የተባለው የJoint Commission ፕሮግራም የጤና ተቋማትን፣ የህዝብ ጤና ኤጀንሲዎችን፣ የጤና ሚኒስቴሮችን እና ሌሎች ተዛማጅ ተቋማትን የታካሚ እንክብካቤን ጥራትና ደህንነት እንዲያሻሽሉ ለመደገፍ የተዘጋጀ ኢኒሼቲቭ ነው። የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ ታካሚዎችና ቤተሰቦቻቸው በራሳቸው የጤና እንክብካቤ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ፣ ጥያቄ እንዲጠይቁ እና ድምፃቸውን በነፃነት እንዲያሰሙ ማበረታታት ነው።

ከ2002 ጀምሮ ፕሮግራሙ በ70 በላይ ሀገራት ለሚገኙ ማህበረሰቦች ተደራሽ ሆኖ በርካታ ዓለም አቀፍ እውቅናዎችን አግኝቷል። የፕሮግራሙ የትምህርት ግብዓቶች በቀላሉ ለማንበብ የተዘጋጁ ኢንፎግራፊክሶችን፣ አጫጭር የትምህርት ቪዲዮዎችን እና እንደ የታካሚ መብቶች፣ የእናቶችና የሕፃናት ጤና፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ቀዶ ሕክምና፣ የአእምሮ ጤና እና የከባድ በሽታዎች መከላከል ያሉ ርዕሶችን ያካትታሉ።

### ዩዝ ፎር ፒስ ኢንተርናሽናል

ዩዝ ፎር ፒስ ኢንተርናሽናል በወጣቶች የሚመራ የሰላም ግንባታ ድርጅት ሲሆን ስልጣን ያላቸው ግለሰቦች እና ዘላቂ ማህበረሰቦች ሰላማዊ ዓለምን ያሳያል። በህንድ ዴሊ ውስጥ የድርጅቱ ሥራ በሦስት ዘርፎች ያተኮረ ነው - የአቅም ግንባታ፣ የመሬት እርምጃ እና ተሟጋችነት። በሙስና እና በወጣቶች፣ በሰላምና በፀጥታ አጀንዳ መካከል ያለው ትስስር ትኩረትን በመምረጥ ልፍል 2 ላይ ተዳስሷል።

### በጋና ብሄራዊ ደህንነት ስትራቴጂ ውስጥ የወጣቶች ተሳትፎ

የጋና ብሔራዊ የደህንነት ስትራቴጂ ወጣቶችን በብሔራዊ የሰላም ምክር ቤት፣ በብሔራዊ አለቆች ምክር ቤት፣ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ ለማሳተፍ የሚያስችል የፖሊሲ ኢኒሼቲቭ ይዟል፤ ይህም ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር፣ የወጣቶችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አቅም ከፍ ለማድረግ እና በጋና ሰላምና ደህንነትን ለማምጣት የታሰበ ነው።

### "የሊባኖስ ሙስናን የሚቃወሙ ወጣቶች"

"የሊባኖስ ሙስናን የሚቃወሙ ወጣቶች" በሊባኖስ በወጣቶች የሚመራ ኢኒሼቲቭ ሲሆን ሙስናን በይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በማህበራዊ ፈጠራ፣ በጋራ ብልህነት እና በሥራ ፈጠራ አማካይነት አስተዋፅኦ ለማድረግ ያለመ ነው።

ሊባኖስ በሀገራቸው የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ተፅእኖ ማሳደር እንችልም ብለው በሚያስቡ ወጣቶች ምክንያት ብዙ አጥታለች። ለዚህም ነው "ሙስናን የሚቃወሙ ወጣቶች" ዋና ዓላማ ወጣቶችን ስለ ሙስና ማስገንዘብ፣ በብሔራዊ ተግዳሮቶች ላይ የራሳቸውን አስተያየት እንዲያዳብሩ ማነሳሳት፣ በመረጃ ላይ የተመሠረቱ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ እና ለዘላቂ ልማት እርምጃ እንዲወስዱ ማበረታታት ነው። ኢኒሼቲቩ ራዕይም በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሙስናን ሰንሰለት ለመስበር የሚደፍሩ ወጣቶችን የሚያሰባስብ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ መፍጠር ነው።

### የYouthLED የቦርድ አባል የኢሳያስ የግል ተሞክሮ

"ገና ልጅ ሳለሁ የተባበሩት መንግስታት ቻርተር በሰብአዊ መብቶች ጥበቃ፣ ሰላምን በማስጠበቅ እና ግጭቶችን በመከላከል ረገድ ስለሚያከናውነው ሥራ ሁልጊዜ እሰማ ነበር። ዩኒቨርሲቲ ስጀምር ጊዜዬን ለበጎ ፈቃደኝነት በመስጠት እና በተባበሩት መንግስታት ሥር ስለሚገኙ የተለያዩ ኤጀንሲዎችና ፕሮግራሞች ጥልቅ ግንዛቤ በማግኘት አላስፈላጊ የሰው ልጅ ስቃይን ለመከላከል ከተባበሩት መንግስታት ጋር የበለጠ ለመስራትወሰንኩ። ይህን ማድረግ ቀላል ያደረገው የተባበሩት መንግስታት ንቁ የማህበራዊ ሚዲያ ተሳትፎ ነበር። ምክንያቱም በተደጋጋሚ በተለያዩ የተባበሩት መንግስታት አካላት የሚዘጋጁ እድሎችን እና ዝግጅቶችን ያሳውቁ ነበር።

በዚህ የኦንላይን ተሳትፎ አማካይነት እ.ኤ.አ. በ2021 ከተካሄደው የጠቅላላ ጉባኤ ልዩ የሙስና መከላከል ስብሰባ ጎን ለጎን የተዘጋጀውን የወጣቶች ፀረ-ሙስና ፎረም ጨምሮ የተለያዩ የወጣቶች ኮንፈረንሶችን ለመከታተል እድል አገኘሁ። በዚህ ዝግጅት ላይ ከ122 አገሮች የተውጣጡ 850 ወጣቶች ኦንላይን ላይ ተሰብስበው ሙስና በወጣቶች ላይ ስለሚያስከትለው ተፅእኖ እና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ወጣቶችን በንቃት እንዴት ማሳተፍ እንደሚችል እንዲሁም የወደፊቱን የፀረ-ሙስና ጥረቶች በመቅረጽና በመምራት ረገድ እንዴት ማበረታታት እንደሚቻል ተወያይተዋል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከYOUNGO ጋር በመተባበር በአየር ንብረት ለውጥ የፖሊሲ ሂደቶች ውስጥ የበለጠ ተሳትፌያለሁ። በ2022 በተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንፈረንስ (COP27) ላይ ለምግብ ሥርዓት ለውጥ ተሟግቻለሁ። እንዲሁም በአቡ ዳቢ በተካሄደው የForeseeing Healthy Futures ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ወጣቶች በትርጉም ያለው መልኩ እንዲሳተፉ ተሟግቻለሁ።"

የመጨረሻ ጠቃሚ ምክር:


# ስራችሁን መገምገምና ያመጣውን ለውጥ ለሌሎች ማሳወቅን አትርሱ

ዘመቻ ስታዘጋጁ ወይም ለውጥ ለማምጣት ያለመ ኢኒሼቲቭ ስትነድፉ ሁልጊዜ ስኬቶቻችሁን፣ ያጋጠሟችሁን ተግዳሮቶች እና ዓላማዎቻችሁን ለማሳካት ያላችሁን አቅም መገምገምና በጥልቀት ማሰላሰል አስፈላጊ ነው። ለአፍታ ቆም ብላችሁ በመገምገም፣ ስትራቴጂያችሁን ለማሻሻል፣ ስኬቶቻችሁን ይበልጥ ለማጠናከር እና ከተግዳሮቶቻችሁ ለመማር ይረዳችኋል።

የሥራችሁን ተጽዕኖ ለመገምገም የሚረዷችሁ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እነሆ:

- ዓላማችሁን ለማሳካት ልታሳኩ የምትፈልጓቸውን ግቦች በግልጽ የሚያስቀምጥ ማዕቀፍ አዘጋጁ።
- ግቦችን መገምገም በመጠናዊም (quantitative) ሆነ በጥራታዊ (qualitative) መረጃ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል።
- ጥራት ያለው መረጃ ለማግኘት፣ ከዘመቻው ወይም ከፕሮጀክቱ አጋሮችና ተሳታፊዎች ጋር በመደበኛነት ዳሰሳዎችንና ቃለ መጠይቆችን በማካሄድ፣ በአፈጻጸሙና በእድገቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት ሰብስቡ።

የቁጥር እና የጥራት ጥያቄዎቻችሁን መንደፍ ለመጀመር ቀላል ማዕቀፍ እዚህ ይገኛል:



“እንዴት?” እና “ለምን?” የሚሉት ጥያቄዎች ስለ ኢኒሼቲቫችሁ የበለጠ ትንታኔያዊ መረጃ በማቅረብ የጥራታዊ ትንታኔ ለማድረግ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

የቃለ መጠይቅ ሂደታችሁ ውጤታማ እንዲሆን የሚረዱ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እነሆ፦

- ከተጠያቂዎች ጋር መተማመንን ማዳበርና እነሱን ማረጋጋት አስፈላጊ ነው። ተጠያቂዎች ድጋፋችሁን ለማግኘት ሲሉ የምትፈልጉትን ምላሽ እንዲሰጡ ጫና ሊሰማቸው ይችላል። ስለዚህ ቃለ መጠይቁ የፀረ-ሙስና ተነሳሽነቱን አፈጻጸም ለማሻሻል የሚያግዝ ቁልፍ የመማሪያ ሂደት መሆኑን እንዲሁም ሙሉ ታማኝነትና ግልጽነት የክትትልና የማሻሻያ ሂደቶችን ለማጠናከር መሠረታዊ መሆናቸውን ግልጽ አድርጉ።
- እንዲሁም ከግለሰብ ተሳታፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ከማድረግ በተጨማሪ፣ ከፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭ እና ከማንኛውም ተዛማጅ ታሪኮች ጋር የተያያዙ ጥቅሶችንና አስተያየቶችን ሰብስቡ። እነዚህን ጥቅሶች፣ አስተያየቶች (እንዲሁም ፎቶዎችን) ለመጠቀም ሁልጊዜ ቅድሚያ ፈቃድ ይጠይቁ።
- ክፍት ወይም ዝግ ጥያቄዎችን ለመጠቀም ይወስኑ። እያንዳንዱ ዓይነት ጥያቄ የራሱ ዓላማ አለው። በአጠቃላይ ዝግ ጥያቄዎች በኢኒሼቲቫችሁ ላይ ተሳታፊዎች ምን ያህል እንደተደሰቱ ለማወቅ ይረዷችኋል። ክፍት ጥያቄዎች ደግሞ ለምን እንደተደሰቱ የበለጠ ዝርዝር መረጃ ይሰጧችኋል።
- መሪ ጥያቄዎችን ከመጠቀም ተቆጠቡ። መሪ ጥያቄዎች መልሱን በውስጣቸው የሚጠቁሙ ጥያቄዎች ናቸው። ስለዚህ በቃለ መጠይቁ ወቅት የተሳታፊዎችን አስተያየትና ምላሽ ሊያዛቡ ይችላሉ።
- የቃለ መጠይቁን ሂደት በተቻለ መጠን ገለልተኛ ያድርጉ። በመርህ ደረጃ መረጃውን የሚሰበስበው ሰው የአዘጋጆች ቡድን አባል መሆን የለበትም፤ ይህም ገለልተኛ አቋም እንዲይዝ ያግዛል። ሆኖም ሪሶርስ ውስን በሆነበት ሁኔታ ይህን ማሳካት ላይቻል ይችላል። በዚህ ሁኔታ ሁሉም ተሳታፊዎች የራሳቸውን አድልዎ እና ከፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቩ ጋር ያላቸውን የግል ትስስር እንዲገነዘቡ እና ገለልተኛ ማበረታታት አስፈላጊ ነው።
- የቁጥር መረጃን ይሰብስቡ። ይህ ማለት አስፈላጊ የሆኑ የቁጥር መረጃዎችን መመዝገብ ማለት ነው። ለምሳሌ የቀረቡ የፖሊሲ ሀሳቦች ብዛት፣ የተደረጉ የማህበረሰብ ቃለ መጠይቆች ብዛት፣ የህግ ማመልከቻዎች ብዛት እና የተሳታፊዎች ብዛት።
- አመላካቾቻችሁን ተፅዕኖን በሚያሳዩ መልኩ ይንደፉ። ጥሩ የቁጥር አመላካቾች ለምሳሌ በዘላቂ ልማት ግቦች (SDGs) ማዕቀፍ ውስጥ ይገኛል። እያንዳንዱ ግብ እድገቱን ለመለካት የሚያገለግሉ አመላካቾች ስብስብ አለው። እነዚህ አመላካቾች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩ በመሆናቸው ሰፊ ቢሆኑም ከእናንተ የፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቭ ጋር እንዲጣጣሙ ማስተካከል ይቻላል። ሆኖም የቁጥር መረጃ ብቻውን ሙሉውን ታሪክ እንደማይናገር ያስታውሱ። ስለዚህ ሁልጊዜ የቁጥር መረጃን ከጥራት መረጃ ጋር ያጣምሩ ወይም በተሰበሰበው መረጃ ላይ የጥራት ትንተና ያካሂዱ።
- የቅህድ የመረጃ ስብስብ ዘዴዎችን ይጠቀሙ። በቁጥር እና በጥራት መረጃ መካከል ለመመጣጠን የተሻለው መንገድ ውህድ ዘዴዎችን መጠቀም ነው። ማለትም የቁጥር መረጃ አሰባሰብን ከጥራት ትንተና ጋር በማጣመር። ይህ የኢኒሼቲቫችሁን ሙሉ ምስል ለማቅረብ የተሻለ እድል ይሰጣል።
- ለክትትል፣ ለግምገማ እና ለመማር የተወሰኑ ጊዜያትን ያቅዱ። ይህን ስራ ምን ያህል ጊዜ መደረግ እንዳለበት የተወሰነ መመሪያ የለም። ሆኖም ግምገማው በኢኒሼቲቩ መጨረሻ ላይ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው መካሄድ አለበት። የመካከለኛ ጊዜ ግምገማዎች ኢኒሼቲቩ በትክክለኛው አቅጣጫ እየተጓዘ መሆኑን ለማረጋገጥ መሠረታዊ ናቸው። ይህም ከግምገማዎቻችሁ በመማር ስትራቴጂያችሁን በተከታታይ የማሻሻልና የማላመድ ሂደት መሆን አለበት።
- ግብረመልስን በተከታታይ ይሰብስቡ። ግብረመልስ መሰብሰብ ከተሞክሮዎቻችሁ ለመማር እና ቀጣይ እርምጃዎቻችሁን ለማሻሻል ይረዳችኋል። በተጨማሪም እናንተንና ቡድናችሁን ሊያበረታታ ይችላል። እንዲሁም ከአጋሮች፣ ከለጋሾች፣ ከዓለም አቀፍ ተዋናዮች እና ከመንግሥታችሁ ጋር ስለፈጠራችሁት ተፅዕኖ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ያግዛል። በማህበረሰባችሁ፣ በሀገራችሁ እና በክልላችሁ ውስጥ ራሳችሁን እንደ ፀረ-ሙስና ሻምፒዮኖች ለማስቀመጥ የትንተናችሁን ውጤት መጠቀም ወደፊት የምታስከትሉትን ተፅዕኖ ያሳድጋል። እንዲሁም ራሳችሁንና ሌሎችን ዓላማችሁን እንዲከተሉ ለማበረታታት ይረዳችኋል። በዚህም ያሰባችሁትን ለውጥ ወደ እውነት ለመቀየር ያግዛችኋል።
- ተፅዕኗችሁን በሰፊው ያጋሩ። የብሎግ ጽሑፎችን እና መጣጥፎችን (ኦንላይንም ሆነ ኦፍላይን) መጻፍ ስለ ተፅዕኗችሁ ግንዛቤን ለማሳደግ ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል። በኮንፈረንሶች እና ኦንላይንም ላይ ዝግጅቶች ላይ መሳተፍም በኔትወርካችሁ ውስጥ ምርጥ ልምዶችን ለማጋራት ጥሩ መንገድ ነው። በመጨረሻም ማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኗችሁን ለማስተላለፍ እና በፀረ-ሙስና ኢኒሼቲቫችሁ ላይ ተመስርተው የጥብቅናና የክትትል ሥራዎችን ለማከናወን በጣም ጠቃሚ መሣሪያ ነው።

# ቀጥሎ ምን አለ?




ለውጥ በባዶ ሜዳ ላይ አይከሰትም። ለውጥ ዑደት ነው፤ እና ትልልቅ ለውጦች በረጅም ጊዜ ውስጥ ብቻ ሊታዩ ይችላሉ። እንደግለሰብ በምታያደርጉት ነገር፣ በጎ ተጽዕኖ በምታሳድሩበት መንገድ፣ በትናንሽ ድሎችም ላይ ማተኮራችሁን አትርሱ። ይህ ኢኒሼቲቫችሁን እንድትጠብቁ ይረዳችኋል።

የአእምሮ እና የአካል ጤንነታችሁን መጠበቃችሁን አረጋግጡ እንዲሁም ለእረፍት በቂ ጊዜ መስጠታችሁን ልብ አድርጉ።

ብቻችሁን ለውጥ ማምጣት ከባድ እንደሆነ አትዘንጉ፤ ስራን በቅልጥፍና ለመስራት በሌሎች ላይ መተማመን አለባችሁ። ፍጥነታችሁን ለመጠበቅ እና ዝቅተኛነት በሚሰማችሁ ጊዜ ተነሳሽነት ለማግኘት በዙሪያችሁ ያለውን ማህበረሰብ እና የድጋፍ ቡድኖች ይገንቡ።

አሁን እየተሰናበትናችሁ አይደለም። ወደ መሣሪያው መጨረሻ ደርሳችሁዋልና እናንተን ለመደገፍ እዚህ መሆናችንን ማወቅ አለባችሁ። የGRACE ድህረገጽ በመደበኛነት በመከታተል ወይም በኢሜይል unodc-grace@un.org በመላክ ያነጋግሩን፤ እናም ይህን ውይይት መቀጠል እንችላለን።

በሕይወታችን ውስጥ ሙስናን ሙሉ በሙሉ ላናጠፋ እንችላለን፤ ነገር ግን በጋራ አስተሳሰባችንን ከሙስና ድርጊቶች ወደ ሥነ ምግባር፣ ታማኝነት፣ ተጠያቂነት እና ግልጽነት መቀየር እንችላለን፤ በዚህም ዓለምን የተሻለች ቦታ ማድረግ እንችላለን!



United Nations
Office on Drugs and Crime

GRACE

YouthLED

**2024 ታተመ**
Vienna International Centre, P.O. Box 500, 1400
Vienna, Austria Tel.: (+43-1) 26060-0, Fax: (+43-1)
263-3389